# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት

(በአዲስ አበባ በተመረጡ ሁለት የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳሪነት)

በ

ሂሩት ዳምጤ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ -ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንፅፅር መፈተሽ፤

(በአዲስ አበባ በተመረጡ ሁለት የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳሪነት)

በ

ሂሩት ዳምጤ

አማካሪ

ጌታቸው እንዳላማው (ዶ/ር)

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎቾ ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድህር ምረቃ መርሀ -ግብር

የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንፅፅር መፈተሽ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ በተመረጡ ሁለት የመንግስትና የግል የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር መርሀ-ግብር ለአርት ማስተርስ ዲግሪ (MEd) ማሟያ በሂሩት ዳምጤ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርስቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለመሟላቱ በፈታኞች ተገራግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ---------------------------------------ፊርማ------------------------ቀን-----------------

የውጭ ፈታኝ---------------------------------ፊርማ-----------------------ቀን----------------

የውስጥ ፈታኝ-----------------------------------ፊርማ------------------ቀን-------------------

# ማረጋገጫ

**የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንፅፅር መፈተሽ ፤** በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎቸ ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በተግባራዊ ስነ-ልሳንና የአማርኛን ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ---------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን ---------------------------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ ላደረሰችኝ ለድንግል ማርያም ክብርና ምስጋና አቀርባለሁ:: ይህ ጥናት እንዲጠናቀቅ እጅግ ትህትና በተላበሰ መልኩ ርዕሱን ከማስተካል ጀምሮ የምሰራቸውን ስራዎች በመከታተል እንዲሁም ተገቢውን እርማትና ማስተካከያ በመስጠት ሙያዊ ድጋፎ ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶክተር ጌታቸው እንዳላማው ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቆይታዬ የተለያዩ ኮርሶችን የሰጣችሁኝ መምህሮቼ ይህ ጥናት የእናንተ ውጤት ነውና ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ በተጨማሪም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጥናቱን ያግዘኝ ዘንድ የገንዘብ በጀት በመመደብ ድጋፍ ስላደረገልኝ አመሰግናለሁ፡፡

ጥናቱን ለመስራት መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስተዋጽኦ ያደረጋችሁልኝ የሥራ ባልደረቦቼ እና ጓደኞቼ፣ እንዲሁም የጽሁፍ ትየባውን ከጎኔ ሆናችሁ ላገዛችሁኝ፣ ሙሉ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ሞራላዊ ድጋፋችሁ እና እገዛችሁ ላልተለየኝ ሁላችሁንም መዘርዘር ባልችልም ፈጣሪ  ያክብርልኝ፤ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አህጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንፅፅር ፈትሿል፡ጥናቱም አወዳዳሪ የምርምር ንድፍን ተከትሏል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ካሉ የግልና የመንግስት ትምህርተ ቤቶች ውስጥ አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ከግል ሆሊሲቨር ትምህርት ቤት ከመንግስት የብርሃነ ኀሊና ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በዚህ ጥናት በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉት በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ወንድ 2 ሴት 2 በድምሩ 4 መምህራን ሲሆኑ እነዚህም በጠቅላይ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም ከእየያንዳንዱ ትምህርት ቤት 36 ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በመጨረሻ በቁጥር መልክ የተሰበሰበውን መረጃ ገላጭ ስታትስቲክስ (በአማካይ፣ መደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ስታትስቲክስ የመተንተኛ ስልት) በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ የግልም ሆነየመንግስትትምህርት ቤት መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች  አተገባበር ዝቅተኛና መሻሻል የሚ ገባው እንደሆነ አመላክቷል፡፡ ከሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪትምህርት ቤቶች መካከል ግን የግል ትምህርት ቤት መምህራን  ከመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር እንዳላቸው በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የአንብቦ መረዳት  ብልሃቶችን ለመተግበር በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር መብዛት እና የተማሪዎች መጽሐፍ ግብአት አለሟላት፣ ወዘተ . ምክንያት የመነጨ እንደሆነ ከተካሄደው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመጨረሻምጥናቱ ለችግሮች የመፍትሂ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠቃሏል፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ማረጋገጫ ........................................................................................ ii
ምስጋና ........................................................................................ iii
አህጽሮተ ጥናት .................................................................................. iv
ምዕራፍ አንድ: መግቢያ .......................................................................... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ .................................................................................. 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................... 3
1.3. የጥናቱ ዓላማ ............................................................................... 6
1.3.1. ዓቢይ ዓላማ ............................................................................. 6
1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ......................................................................... 6
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት .......................................................................... 7
1.5. የጥናቱ ወሰን ................................................................................ 7
1.6 ውስንነት ...................................................................................... 8
ምዕራፍ ሁለት: የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ ........................................................ 9
2.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት ................................................................... 9
2.2. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ዓላማ ......................................................... 10
2.3. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ጠቀሜታ ...................................................... 10
2.4. አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ምንነትና ሲዘጋጁ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች ............... 11
2.5. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነት .......................................................... 12
2.6. የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች ............................................. 13
2.6.1 የቅድመ ንባብ ተግባራት ................................................................... 14
2.6.2 የንባብ ጊዜ ተግባራት ..................................................................... 15
2.6.3 የድህረ ንባብ ተግባራት ................................................................... 17
2.7. የአንብቦ መረዳት ትምህርትን የማስተማሪያ ብልሃቶች ....................................... 18
2.8. የንባብ ትምህርትን ለመተግበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የመጠቀም ሚና ............................................. 32
2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት ................................................................... 33
ምዕራፍ ሦስት: የአጠናን ዘዴ .................................................................... 37
3.1. የጥናቱ ንድፍ ............................................................................... 37
3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ..................................................................... 37

3.2.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........ 37
3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 38
3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 38
3.2.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 38
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 39
3.3.1 የክፍል ምልከታ ........ 39
3.3.2 የፅሁፍ መጠይቅ ........ 40
3.3.3 ቃለ መጠይቅ ........ 40
3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 41
ምዕራፍ አራት: የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ........ 42
4.1 የተጠኘ መምህራን ዳራዊ መግለጫ ........ 42
4.2 የተጠኘ ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ ........ 43
4.3. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ........ 43
4.3.1. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር በቅድመ ንባብ ደረጃ (ከምልከታ አንፃር) ........ 44
4.3.2. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በጊዜ ንባብ ደረጃ (ከምልከታ አንፃር) ........ 47
4.3.3. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በድህረ ንባብ ደረጃ (ከምልከታ አንፃር) ........ 50
4.4. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ጠቅላላ ውጤት (ከምልከታ አንፃር)... 52
4.4.1. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር).... 53
4.5 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ማብራሪያ ........ 59
4.6. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 62
ምዕራፍ አምስት ........ 64
ማጠቃለያ እና አስተያየት ........ 64
5.1 ማጠቃለያ ........ 64
5.2. አስተያየት ........ 66
ዋቢ ፅሁፎች ........ 68
አባሪ አንድ ........ 73
አባሪ ሁለት ........ 76
አባሪ ሶስት ........ 79

## የሰንጠረዥ ማዉጫ

ሠንጠረዠ 4.1 የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ.......................................................42
ሠንጠረዠ 4.2 የተጠኝ ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ.........................................................43
ሠንጠረዥ 4.3: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች (በቅድመ ንባብ ደረጃ).................................44
ሰንጠረዥ 4.4: በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ....................45
ሠንጠረዥ 4.5: ቲ ቴስት (በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ).......................................................................................46
ሠንጠረዥ 4.6: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በጊዜ ንባብ ደረጃ.....................................47
ሠንጠረዥ4.7: በጊዜ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር .........................49
ሠንጠረዥ 4.8: ቲቴስት (በንባብ ጊዜ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ)........................................................................................49
ሠንጠረዥ4.9: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በድህረ ንባብ ደረጃ......................................50
ሠንጠረዥ 4.10 በድህረ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ....................51
ሠንጠረዥ 4.11 ቲ ቴስት (በድህረንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ ........................................................................................52
ሠንጠረዥ4.12 ቲ ቴስት (በሁሉም ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ ........................................................................................52
ሠንጠረዥ 4.13: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በቅድመ ንባብ ደረጃ (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)...................................................................................................53
ሠንጠረዥ 4.14 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በጊዜ ንባብ ደረጃ.....................................55
ሠንጠረዥ 4.15: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በድህረ ንባብ ደረጃ.................................57
ሠንጠረዥ 4.16 ቲ ቴስት (በሁሉም ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር).......................................................59

# ምዕራፍ አንድ: መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ንባብ ለተማሪዎች ማስተማር ከቃላት አነባበብ ጀምሮ የንባብ ሃሳብን ከፅሁፉ እንዲረዱ አስከማድረግ ድረስ ያሉ ሁኔታዎችን ሊያጠቃልል እንደሚችል Nuttall (1982) ገልፀዋል፡፡ ይህ ክሂል አእምሯዊ ሂደትን በውስጡ ስለሚያጠቃልል ውስብስብ እንዳሰኘው ደበበ (2008) ይጠቁማል፡፡

Rubin (1987) እንደገለፁት ስለብልሃቶች ጥናት የተጀመረው Aaron carton የተባሉ ምሁር እ.አ.አ. 1966 ዓ.ም፡፡ በውጭ ቋንቋ ጥናት ሃሳብ ፈልፍሎ የማውጣት (infelence) ዘዴ በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ካሳተሙ በኋላ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናትተማሪዎች ሃሳብ ፈልፍሎ በማውጣት ረገድ ባላቸው ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ እና ጠቃሚ ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ በሆነ ሃሳብ ፈልፍሎ የማውጣት ችሎታቸው እንደሚለያዩ ይለያያሉ፡፡

እንደ Block (1997) አገላለፅ ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አንባቢዎች ፅሁፉን እንዴት አንብበው እንደሚረዱ ፅሁፉን ባልተረዱ ጊዜ ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ Baker& Boonkit(2004) የማንበብ ሂደት የተለያዩ ብልሃቶችን በመተግበር በንቃት መሳተፍን የሚጠይቅ ነው፡፡

ታደሰና ሌሎች (2010) Sehunk (2012)ን እና Zimmerman (2002)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ደግሞ ተማሪዎች ግንዛቤያዊ፣ ልዕለ ግንዛቤያዊና የሃብት አጠቃቀም የራስ መር ብልሃቶችን ለመማር ዑደታዊ ሂደትን ይተገብራሉ፡፡ በዚህም ራስን የመምራትና በራስ መሪነት የመማር ችሎታ እያደገ ይመጣል፡፡ተማሪዎች ራስን የመምራት ችሎታና አዳዲስ ተግባራትን የመተግበር ብቃት ብልሃቶችን ከማሰልጠን ይመነጫል፡፡በነዚህ ሂደቶች ያለፉ ተማሪዎች በሂደቱ ካላለፉት በጉልህ ደረጃ ውጤታማና በርካታ የምንበብ ብልሃቶችን የሚጠቀሙ፣ለረጅም ሰዓታት በርካታ ፅሁፎችን ማንበብና መረዳት የሚችሉ ሁሌም በራሳቸው የሚነሳሱ ተማሪዎች ይሆናሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን በሰጡት ገለፃ መሰረት፣ ብልሃቶች የሚባሉት የመማር ስልቶች ፣ባህሪዎች፣ተግባሮች ወይም እርምጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው መረጃ በማግኘት መረጃውን በአእምሮ ለማስቀመጥና በተፈለገ ጊዜ መልሶ ለመጠቀም ያስችላል፡፡በመሆኑም ብልሃቶች ተማሪው ቋንቋውን በመማር ሂደት የገጠመውን ችግር ለመፍታት መርጦ የሚገለገልባቸውና በራሱ ቁጥጥር የሚመራባቸው ናቸው፡፡

ማንበብ ፈርጀ ብዙ ችሎታዎችን በተመሳሳይ ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ የአንድን ፅሁፍ መልዕክት መረዳት ወይም መተርጎምን የሚጠይቅ ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም ክሂሉን ለማጎልበት መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከክሂል ባሻገር የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ማስተማር እንደሚጠበቅባቸው Wenden (1991) ያስገነዝባሉ፡፡ Oxford (1990) እንደሚሉት የመማር ብልሃቶችን በተማሪዎች ሆን ተብለው የሚመረጡ መማርን ለማፋጠን ወይም ስለቋንቋውመረጃን ለማካበት ፣ለማስታወስና በተግባር ለመጠቀም የሚያገለግሉ ሂደቶች ናቸው፡፡ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ናቸው፤ቀላል አዝናኝ ነገሮችን በራስ ተነሳስቶ በማስተካከል ወደ አዲስ ዕውቀት ለመሸጋገር የሚያስችሉ ተግባራትም ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የመማር ብልሃቶች ቀላልም ሆነ ከባድ ተግባራት ተማሪዎች ሲገጥሟቸው የተለየ ጉልበትና ጊዜ ሳያወጡ እንደ መማር ብልሃቶች ምርጫቸው የሚያከናውኑባቸው ብልሃቶች ናቸው፡ ይህም ተማሪዎች የአንድን ትምህርት ዓላማ ግብ የሚያደርሱበት መንገድ ነው፡፡ እንደ Willing (1989) ገለፃ ተማሪዎች ብልሃቶችን በግልፅ መማራቸው ለምን አስፈለገ ለሚለው ጥያቄ ከውስብስብነቱ ባሻገር ለጥያቄው እንደ ምላሽ ያቀረቡት እንደ ብልሃቱ ዓይነት እንደ ተማሪዎቹ የመማር ምርጫ ፣የመነቃቃት ሁኔታ እና ያታ ሊለያይ እንደሚችል የሚጠቁም ነው፡፡

Omalley & Chamot (1990) ይሽንኑ ሃሳብ የሚጋሩት ሲሆን የብልሃቶች አቀራረብ ምርጫ በተማሪዎች ባህሪያት እንደሚወሰን አመላክተዋል፡፡ እንዲሁም መምህራን በክፍል ውስጥ ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች መካከል ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች እንዳሉ በመጠቆም ችግሮቻቸውም የማንበብ ብልሃቶችን አለመጠቀማቸው ነው፡፡

Oxford & Crookali (1989) የመማር ብልሃቶች የሚባሉት የመማር ስልት ፣ባህሪ፣ ተግባር ወይም መማር ፣ችግር መፍታት ፣የጥናት ክህሎት ሊባሉ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡ ስያሚያቸው ምንም ይሁን ምን ብልሃቶች መማርን በጣም ብቃት ያለውና ውጤታማ ማድረግ የሚችሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት ምሁራን በሰጡት ገለፃ መሠረት፣ብልሃቶች የሚባሉት የመማር ስልቶች፣ባህሪዎች፣ተግባሮች ወይም እርምጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው መረጃ በማግኘት መረጃውን በአእምሮው ለማስቀመጥ እና በተፈለገ ጊዜ መልሶ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ በመሆኑም ብልሃቶች፣ተማሪው ቋንቋን በመማር ሂደት የገጠመውን ችግር ለመፍታት መርጦ የሚገለገልባቸውና በራሱ ቁጥጥር የሚመራባቸው ስልቶች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ብልሃቶች መማርን በቀላል፣ ፈጣንና ስኬታማ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና ያላቸው ስልቶች ናቸው፡፡

ከላይ የተገለፀው ንድፈ ሃሳብ እንደሚያመለክተውና የዚህ ጥናት አቅራቢም ከተሞክሮዋእንደተገነዘበችው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን አለመጠቀም እንደምክንያትነት መጠቀሱ ነው፡፡ በተለይ ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች እንዲህ ዓይነት ቸግር መኖሩን ትምህርት ቤቶቹ በሚገኙባቸው አከባቢ የሚገኝ ትምህርት ጽህፈት ቤት በአንድ ወቅት ባከናወነዉ ስልጠና ላይ የገተለጸበት አጋጣሚ ነበ ፣ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈትቤት,(2022)፡፡

ይህ ጥናት ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ባሉ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በየትኞቹ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ችግሮች እንዳለባለቸው ነቅሶ ከማውጣት ባሻገር በትምህርት ቤቶቹ መካከል የጎላ የንባብ አተገባበር ልዩነት ስለመነኖሩም ይሁን ስለአለመኖሩ ፈትሿል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንዳንድ ምሁራን ለተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ማስተማር ተገቢ ነው ቢሉም አንዳንዶች ደግሞ የመምህራን ተግባር ሁኔታዎችን ማመቻቸትና አቅጣጫ ማመላከት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

Norton(1997) የጥናት ውጤቶች የሚያመለክቱት በአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ውስጥ ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ችላ መባላቸው አንብቦ የመረዳት

ችግርን ለማቃለል መሰናክል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ Williams & Burden (1997) ከዚህ በፊት የነበረው የትምህርት ሂደት የብልሃቶችን አጠቃቀም ማሰልጠን ወይም ማዳበር ችላ ያለ እንደነበር አስገንዝበዋል፡፡ Shang (2010) ጥናት ተማሪዎች በንባብ አውድ ውስጥ የብልሃት እውቀታቸውን አተገባበር ካልተማሩ የብልሃት ዕውቀታቸው ብቻ የንባብ ውጤታቸውን ስኬታማነት እንደሚቀንሰው ገልፀዋል፡፡

በተቃራኒው ብልሃቶችን መማር ያለውን ጠቀሜታ አስመልክቶ የሚስማሙ ፀሐፍት እንዳሉ ሁሉ የማይስማሙም አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Sandra (1994) ሲሆኑ መምህራን ተማሪዎች የሚያነቡትንና የሚያነቡበትን ብልሃት በራሳቸው የሚመርጡበት እንዲሁም የሚያጠኑበትን አካባቢ ማመቻቸት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ Krashen & terrel (1983) Sliberstein (1994) የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር በኩል መምህራን ጣልቃ መግባት እንደሌለባቸው በመጠቆም የአብዛኞቹ መምህራን ድርሻ ተማሪዎቹ የሚያነቡትንና የሚያነቡትን ብልሃት ሁኔታና አካባቢ ማመቻቸት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡Omally & Chamot (1990) የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ምንነት ዓይነትና ጠቀሜታ ሳይረዱ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በተከታታይ እንዲሰሩ የተደረጉ ተማሪዎች የብልሃቱን ምንነትና ጠቀሜታ ከተማሩት የተሻለ የአንብቦ መረዳት ውጤት ለማግኘት ችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ልዩነቱ የጎላ እንዳልነበር አመላክተዋል፡፡

በአጠቃላይ በአንብቦ መረዳት ብልህቶች ዙሪያ የተካሄዱ እነዚህ ጥናቶች ብልሃቶችን ካልተማሩ የብልሃት ውጤታቸውን እንደሚቀንስና ብልሃቶችን ማስተማር አስፈላጊ አይደለም ያልተማሩት ከተማሩት የተሻለ ውጤት አምጥተዋል የሚሉ ጥናቶች ልዩነት በብልሃቶች ዙሪያ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያሳያሉ፡፡

ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ኖሯቸው አንብበው መረዳት እንዲችሉ በመማር ብልሃቶች በመታገዝ ማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን Pearson (2009) ይገልፃሉ፡፡ አንብቦ መረዳት የሚቻለውም ሆነ ለማንበብ ተነሳሽነት የሚኖረው ውህድ አሃዱ የሚቀርብበትን መቼት መሠረት በማድረግ ጥልቅና በብልሃቶች ላይ የተመሰረቱ አቀራረቦችን በመጠቀም መሆን እንዳለበት ያብራራሉ፡፡ ተማሪዎች የራሳቸውን መማር በራሳቸው በመመራትና በማከናወን ጥሩ የአንብቦ መረዳትና የማንበብ

ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ቀዳሚ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

እንዲሁም እንድሪስ አባይ (2009) ባጠኑት ጥናት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የተወሰነ ግንኙነት ያለው ቢሆንም ይህ ጥናት ግን የሚያተኩረው በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ በንፅፅር በ8ኛ ክፍል ደረጃ መቃኘት ነው፡፡

በመሆኑም አጥኚዋ ይህ ክፍተት መኖሩን በመገመት ለችግሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ በአእምሮዋ በማመላለስ ጥናት ለማድረግ የተነሳሳች ሲሆን የተማሪዎች አንብቦ መረዳት እንዳይዳብር ያደረጉ እንቅፋቶችን መለየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በተጨማሪም የዚህ ጥናት አቅራቢ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት በሰራችባቸው ዓመታት ከመምህራን ጋር ባደረገችው የልምድ ልውውጥ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ላይ ክፍተት መኖሩን ታዝባለች፤ የግል ትምህርት ቤት መምህራንስ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከመፈለጓም በተጨምሪ በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዴት እንደሚተገብሩ ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ስላላት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የጥናቱን ግኝት በመፈተሽ ጠንካራ ጎኖች የሚጎለብቱበትንና መሻሻል የሚገባቸው ተግባራት የሚሻሻሉበትን የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመጠቆም ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ለሚከተሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ከፍ ለማድረግ የትኛውን የአንብቦ መረዳት ብልሃት ተጠቅመው ያስምራሉ?

2. የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል መልመጃዎችን ከሚስማሙ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ጋር አገናዝበው ያስተምራሉ?
3. የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ይዘቶችን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ይጠቀማሉ?
4. የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የንባብ ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ምክንያቶች ይኖሩ ይሆን?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1. ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የግልና የመንግስ ት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የ አንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባር በንፅፅር መፈተሽ ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

1. በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የንባብ ክሂል ከፍ ለማድረግ የትኛውን የአንብቦ መረዳት ብልሃት ተጠቅመው እንደሚያስተምሩ በንፅፅር መፈተሽ።
2. በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ከሚስማሙ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ጋር አገናዝበው ማስተማራቸውን በንጽጽር መመርመር።
3. በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ይዘቶችን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ እያበረታቱ ማስተማራቸውን በንፅፅር መመርመር።
4. በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ

መምህራን የንባብ ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ምክንያቶች መኖራቸውን በንፅፅር መፈተሽ።

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በግልና በመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንፅፅር በመፈተሽ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የተሻለ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በክፍል ውስጥ እንዲከተሉ የሚያስችል ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ጥናቱ በአጠቃላይ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለሚያዘጋጁ አካላትና ተቋማት የተሻለ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ለመተግበር የሚጠቅሙ ነገሮችን ይጠቁማል፡፡

በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ በተመሳሳይ ጥናታቸውን ለሚያደርጉ አጥኚዎች እንደመነሻ ግብዓት በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አኳያ ትኩረት ያደረገው በ2015ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ በሚገኙ የብርሃነ ኀሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ የመንግሰት ትምህርት ቤት እንዲሁም ከግል ሆሊሴቨር ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንጽጽር መፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህ ችግር በሌሎች ትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ቤቱ ውስጥም በሚገኙ በሌሎች የክፍል ደረጀዎች ሊኖር ቢችልም ከጊዜ ውስንነት (እጥረት) የተነሳ ከአጥኚዋ የስራ ቦታ አንጻር በተመረጡት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ሌሎች ክሂሎችን አትመለከትም፡፡

## 1.6 ውስንነት

ጥናቱ የመምህራንን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በንጽጽር የሚፈትሽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ስር በሚገኙ ሁለት የመንግስትና የግል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ከመሆኑ የተነሳ በክፍለ ከተማው የሚገኙ ሌሎች አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አለማካተቱና በስምንተኛ ክፍል ብቻ ትኩረት ማድረጉ ጥናቱ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ውስንነት ሊታይበት ችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት: የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ

## 2.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ማለት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚተላላፈውን መልዕክት መገንዘብ እና ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ሲሆን፣ ጥልቅ ግንዛቤን የሚጠይቅ ነው፡፡ አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈልገውን መረጃ የሚለይበት ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤን የሚመለከት ነው፡፡ በማለት Williams (1997) ገልፀዋል፡፡

ማረው (1998) አንብቦ መረዳት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለጹ “ አንድን ፅሁፍ አንብቦበውስጡ ሊተላላፍ የፈለገውን መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብን ያመለክታል” ይላሉ፡፡ዘርዘር ተደርጎ ሲታይም አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ምንባብ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት ማሰባሰብ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ሂደት ውስጥ አንባቢው የማያስፈልገውን መረጃ እያንገዋለለ በመተው የሚፈልገውን ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡ ከዚህም በላይ የአንድን ምንባብ መሰረታዊ ሃሳብ ከመረዳቱም ባሻገር የምንባቡን ዝርዝር ሁኔታ በብቃት መገንዘብ የሚቻለው በዚሁ አንብቦ በመረዳት ውስጥ ይጠቃለላል በማለት ሀሳቡን አጠናክረውታል፡፡

Shanehan(2006) እንደገለፁት አንብቦ መረዳትን በሁለት ይከፍሉታል አንደኛ በምንባቡ ውስጥ በግልፅ የሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳት ነው፡፡ በዚህ ስርም በፅሁፉ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦች መገንዘብ በግልፅ የተቀመጡ ድርጊቶችን፣ ክስተቶችና ቅደም ተከተል ማስታወስ በፅሁፉ ውስጥ የሰፈሩ ተመሳሳይና ልዩነቶችን መለየትና የምክንያትና የውጤት ትስስር መግለፅን ያካትታሉ፡፡ ሁለተኛ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በምንባቡ ውስጥ በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ ይጠቁማል፡፡ ይህ ዓይነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ መለየትንና ደጋፊ ሀሳቦችን ለይቶ ማወቅን ከምክንያትና ውጤት ትስስር የተነሳ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ነገር መገመትን የሚመለከት ነው፡፡

## 2.2. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ዓላማ

ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ ለምን ዓላማ ሲሉ ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳወቅ የተለያዩ ምንባቦችን በማስነበብ ልምዱን ማስጨበጥ አስፈላጊ ነው፡፡

Mei-Yun (1993) እንዳብራሩት የንባብ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ ጥሩ የንባብ ችሎታ ያላቸውን አንባቢዎች ማፍራት ነው፡፡ በተጨማሪም መሠረታዊ የመረዳት ችሎታን በማሳደግ የምንባበቡን አጠቃላይ ሀሳብ አንብቦ ለመረዳት፣ በማንበብ አጠቃላይ እውቀትን ለማሳደግ የሚነበብበትን ዓላማ ለመወሰን፣የንባብ ዘዴንም እንደ ሁኔታው ለመለወጥ እና ሂሳዊ የማንበብ ችሎታን ለማዳበር ያስችላል በማለት ገልጸዋል፡፡

Wallace (1992) ሰዎች ንባብ የሚያነቡበትን ዓላማ በሦስት በመክፈል ይመለከቷቸዋል፡፡እነሱም፡- ንባብ ለህልውና ዓላማ፣ንባብ ለመማር ዓላማና ንባብ ለመዝናናት ዓላማ የሚሉት ናቸው፡፡ Davis (1995) በበኩላቸው የንባብ ዓላማዎችን በዝርዝር በመመልከት በአምስት ይከፍሏቸዋል፡፡ እነርሱም፡- ምንባብ ለመዝናናት ዓላማ፣ ንባብ የፅሁፍን ላዕላይ ገፅታ ለማወቅ ዓላማ ፣ ንባብ ንባብንና ጥናትን ለማደራጀት ዓላማ፣ ንባብ ይዘትን (የአሰራር ቅደም ተከተልን) ለማወቅ ዓላማ እና ንባብ ለመማር ዓላማ የሚሉት ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ Harmar (2001) ደግሞ የንባብ ዓላማን በሁለት በመክፈል ንባብ አገልግሎት ሰጪነት እና ለመዝናናት ዓላማ በማለት ይገልጿቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የንባብ ክሂል ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች እንደየዓላማቸው እና እንደ ፅሁፉ አይነት የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው ማንበብ እንዲችሉ፣አስተማማኝ የቋንቋ ብቃት እንዲኖራቸው፣ የተፃፉ ጉዳዮችን በተገቢው መንገድ እንዲረዱ እና አንድ ፅሁፍ ወይም ዓረፍተ ነገር በተለያየ አውድ ውስጥ የተለያየ መልዕክት ሊኖረው እንደሚችል እንዲገነዘቡ ማስቻል ነው፡፡

## 2.3. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ጠቀሜታ

Davis (1995) ንባብ ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገልፁ “ንባብ ከሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች በተሻለ መንገድ አለምን ለማሰስ እና ራስን ከሰፊው ዓለም ጋር ለማስተዋወቅ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ማለት ንባብ ማህበራዊ፣ ባህላዊና አካዳሚያዊ አድማስን ያሰፋል ማለት ነው”ይላሉ፡፡

በተጨማሪም Nutall (2000) "ንባብ ፀሀፊው በስራው ውስጥ ያሰፈረውን ቁም ነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ ተደራሲው በንባብ ሂደት የፅሁፉን ፍሬ ሃሳብ ለመረዳትና አስፈላጊ መረጃን ከውስጥ ለይቶ ለማውጣት የፀሐፊውን ሃሳብ ይመረምራል፡፡ ስለዚህ ንባብ የሌሎችን ሃሳብ ለመረዳት እንዲሁም ለመግባባት ዓላማና ሂደት ወዘተ. የምንጠቀምበት ተግባር ነው" በማለት ይገልፃሉ፡፡

እንደ Harmar (1991) ንባብ ከተቀባይ ክሂሎች የሚካተት ሲሆን ፣ ከምናነበው ፅሁፍ ውስጥ ቁም ነገሩን ነቅሶ ለማውጣት የምንባቡን ዝርዝር ሃሳብ ለመረዳት ወዘተ. አጠቃሎ የያዘ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ይህም ንባብ በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የቀረበን ቁም ነገር አንብቦ ለመረዳት የሚጠቅም መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ሚና ያለው ክሂል ነው፡፡በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች፣ መረጃ የመሰብሰብና አዲስ እውቀት የማግኘት፣ ለፈተና፣ ለመማር፣ አሳይመንቶችንና ፕሮጀክቶችን ለመስራት ወዘተ.ያነባሉ፡ ፡ የተማሪዎችንም አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሻሻል በተለያዩ መንገዶች የሚደረጉ ጥረቶች፣ የተማሪዎችን የትምህርት ስኬትን ለማሻሻል እንደመፍትሄ ይቆጠራሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ በከፍተኛ ደረጃ፣አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ማተኮር እንዳለባቸውም አክለው ይገልፃሉ፡፡

## 2.4. አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ምንነትና ሲዘጋጁ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች

Davis (1995) ቋንቋን ለማስተማር ዓላማ ባደረገ የንባብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መመለስ እንዲያስችላቸው መምህራን በቅድመ ንባብ ተግባራት ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲፈትሹ ያደርጋሉ፡ ፡ የሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍትም ይህን የተከተሉ ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም በቅድመ ንባብ ተግባር የተፈተሹ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት፣ በንባብ ጊዜ የሚያዙ አጫጭር ማስታወሻዎችን ካነበቡ በኋላ የሚካሄዱ ውይይቶችን፣ የፅሁፉ ተግባራትና ሌሎች ክሂሎችን አጠቃለው የሚይዙ ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች መሠረታዊ የሆኑ በይዘት ላይ ያተኮሩ መልመጃዎችን እንዴት እንደሚሰሩ በመጠቆም ልምድን ያዳብርላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የአንድን ፅሁፍ አጠቃላይ መልዕክት ከተለያዩ አስተያቶች አንፃር መገንዘብን ለመመርመር የሚዘጋጁና ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ መንገድን የሚያሳዩ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ በርካታ ነጥቦች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የአንባብያንን ችሎታ በመመዘን ላይ ብቻ ያተኩሩ ሳይሆኑ አንባብያኑ አንድን ፅሁፍ ለመረዳት በራሳቸው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ስልት እንዲቀይሱ የሚገፋፉ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ በርካታ ነጥቦች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱትን Grellet (1981) ገልፀዋል፡፡ እነሱም፡- ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመር፣የጥያቄዎችን ስብጥር መጠበቅ፣ ከልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀት በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ናቸው፡፡

## 2.5. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነት

Ardasheava & Tretter (2013) እና ElEssawi እንደሚያስረዱት የመማር ብልሃቶችን ርቱዕ እና ኢ- ርቱዕ ብለው በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ የመማር ብልሃቶች ከቋንቋው መረጃ ጋር በቀጥታ ተራክቦ በማድረግ የሚያገለግሉትን ሲሆን በውስጡ ትውስታ ብልሃት፣ አእምሯዊ ብልሃትና የማካካስ ብልሃትን ይይዛሉ፡፡ የትውስታ ብልሃት(memory strategy) የመመደብና ምስል የመፍጠር ብልሃቶችን የሚመለከት ነው፡፡ አዕምሯዊ ብልሃት(cognitive strategy) ከቀረበው አዲስ የቋንቋ መረጃ ጋር ተራክቦ ለማድረግ የሚያስችሉ ሲሆን እንደ መተንተን፣ ማጠቃለልና ልምምድ ማድረግን የመሳሰሉ ንዑሳን ብልሃቶችን አካቶ ይይዛል፡፡ የማካካስ ብልሃት (compensation strategy) ደግሞ ተማሪዎች በስነ - ልሳን ዕውቀታቸው ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያግዙ እንደ መገመትና ተመሳሳይ ቃላት ፍችን መጠቀም የሚሉትን ንዑሳን ብልሃቶች እንደሚይዝ ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል ኢ- ርቱዕ ብልሃቶች፣ ተማሪዎች የራሳቸውን መማር ማደራጀት እንዲችሉ የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው፡፡ ይህ ምድብ ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃትን፣ ስሜታዊ ብልሃትንና ማህበራዊ ብልሃትን በስሩ ያካትታል፡፤ልዕለ አዕምሯዊ

ብልሃት የቋንቋ ተግባራትን በመከዎን ማቀድና ራስን መገምገም የሚያስችሉ ብልሃቶችን የያዘ ነው፡፡ ስሜታዊ ብልሃት ጭንቀትን መቀነስና ራስን ማበረታታት የሚሉ ብልሃቶችን ያቅፋል፡፡ ማህበራዊ ብልሃት፣ከጓደኞች ጋር በክፍል ውስጥ የሚደረግን መስተጋብር ወይም ከአፊ- ፊት ተናጋሪዎች ጋር መራከብ የሚሉ ስልቶችን የሚያጠቃልል ብልሃት እንደሆነ በፅሁፋቸው አሳይተዋል፡፡

Parra (2007) በብልሃት ጥናት መስክ ቀዳሚ የሆኑት ምሁር Rubin (1987) መሆናቸውን በመጥቀስ ቋንቋ የመማር ብልሃቶቹን በሁለት አብይ ክፍሎች ይከፍሏቸዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርት እድገት ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ያላቸውንና በተማሪው የሚዋቀሩትን ብልሃቶች ርቱዕ ብልሃቶች ይሏቸዋል፡፡ በዚህ ብልሃት ስር አዕምሯዊና ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃቶች ይካተታሉ፡፡

አዕምሯዊ ብልሃቶች ቀጥተኛ የሆነ ትንተናን፣ ሽግግርን፣ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ማደራጀትን የሚፈልጉና በመማር ወይም ችግር በመፍታት ሂደት ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ እርምጃዎች ወይም ክዋኔዎች ናቸው፡፡ ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃቶች ደግሞ የቋንቋ መማርን፣መገንዘብን፣የመቆጣጠር ወይም በራስ የመምራት የሚያገለግሉ ብልሃቶች ናቸው፡፡ ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች የመማር ሂደቱ ኢ- ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው ብልሃቶች ሲሆኑ በዚህ ስር የተግባቦት ብልሃቶችና ማህበራዊ ብልሃቶች እንደሚጠቃለል አመልክተዋል፡፡

## 2.6. የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች

መምህራን ከመማሪያ መጻሕፍትም ሆነ ከሌሎች ቅንጫቢዎች አንብቦ መረዳትን ሲያስተምሩ ሦስት (3) ደረጃዎችን እንደሚተገብሩ የተለያዩ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ እነዚህም ተግባራት ቅድመ ንባብ ተግባራት፣ ጊዜ ንባብ ተግባራት እና ድህረ ንባብ ተግባራት እንደሆኑ ይታያል (2003)፣ Williams (1984) በድሉ (2007)፣ ማረው እና ሰፉ (2000) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን እነዚህን ተግባራት ማከናዎን አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ ተግባራት በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.6.1 የቅድመ ንባብ ተግባራት

መምህራን ለትምህርት የቀረበውን አሃድ ከማስነበባቸው በፊት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎችም ለምንባቡ ዝግጁ የሚሆኑበት ነው፡፡ ይታያል (2003፣12) Harmer (1990)ን ጠቅሰው ሲያስቀምጡም ይህ ደረጃ ተማሪዎች እና መምህራን ለዋናው ትምህርት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት እና ከምንባቡ ጋር የሚተዋወቁበት ነው» ብለዋል፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ በድሉ (2007፣47-48) ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል፡

አብዛኛውን ጊዜ ንባብ የምንጀምረው በባዶ ጭንቅላት አይደለም፡፡ ስለምናነበው ጉዳይ የተወሰነ ነገር፣ሃሳብ ወይም ጥያቄዎች ይኖራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የምናነበውን ሃሳብ በተመለከተ መላምቶች ይዘን ማንበብ እንጀምራለን፡፡ እንደዚህ አይነት መላምቶች፣ ግምቶች እና ጥያቄዎች ለንባባችን ምክንያት ይፈጥራሉ፡፡ ምክንያት ደግሞ የፍላጎት ምንጭ ነው፡፡ መላምቶችን እና ግምቶቻችንን ለማረጋገጥ ጥያቄዎቻችንን ለመመለስ ስለምንጥር ትኩረታችን በምናነበው ነገር ላይ ይሆናል፡፡

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው በቅድመ ንባብ ተግባራት የተለያዩ ጥያቄዎችን ይዘን መነሳታችን የንባብ ፍላጎታችንና የማወቅ ጉጉታችን ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ተማሪዎች ምን ላይ አተኩረው ንባባቸውን ማድረግ እንዳለባቸው ፍንጭ ስለሚሰጥ ለሌሎች ደረጃዎች መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ደረጃ ላይ የሚከተሉትን ተግባራት አስቀድሞ ማከናዎን አስፈላጊ እንደሆነ በድሉ (2007) እንዲሁም ማረው እና ሰፉ (2000) ይገልጻሉ፡፡

**ዳራዊ እውቀትን ማነቃቃት** (መቀስቀስ)፡- ተማሪዎች የሚያውቁትን ሁሉ አስታውሰው አሁን በሚማሩት ላይ እንዲተገብሩት ማድረግ ነው፡፡

**ዳራዊ እውቀትን መገንባት(ማጎልበት)፡-** ዳራዊ እውቀታቸው ደካማ ከሆነ ከምንባቡ ውስጥ የተወሰኑትን መርጦ በማስረዳት ማሟላት እና ማጠናከር ይቻላል፡፡

**ስለሚነበበው ቅንጫቢ (ጽሁፍ) የተወሰነ** ግንዛቤ (እውቀት) መፍጠር፡- በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን መሰረታዊ እና ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦች ፣ቃላት ድርጊቶች፣የጽሁፍ አወቃቀር እና ወዘተ ማሳወቅ አለበት፡፡

**የቃላት እውቀት አቅምን ማሳደግ፡-** ጽሁፉን ለመረዳት በጣም አስፈላጊ እና ወሳኝ የሆኑ ቁልፍ ቃላት በመለየት ለተማሪዎች ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

**ጽሁፉ የሚነበብበትን ዓላማ መንደፍ እና አቅጣጫ** ማሳየት፡- ጽሁፉ የሚነብብበትን ዓላማ ካስረዳናቸው በንባብ ሂደት ላይ የት ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

**ስለጽሁፉ አነባበብ መመሪያ** መስጠት፡- ይህ የሚሆነው ተማሪዎቹ ትንበያቸውን ካከናወኑ በኋላ ነው፡፡

**አዳዲስ ቃላትን ማቅረብ፡-** ተማሪዎች ከዚህ በፊት የማያውቋቸውን ቃላት ከአነባበባቸው ወይም አውዳቸው እንዲረዱ ሁኔታዎችን አመቻችተን በንባብ ጊዜ በቃላት ላይ እንዲያተኩሩ እና ፍቻቸውን እንዲረዱ ያስችላል፡፡ የሚቀርቡት ቃላት ግን ሁሉም እንዳልሆኑ በድሉ (2007) ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ የቅድመ ንባብ ተግባር ተማሪዎች መርጠው እንዲያነቡ እድል ያመቻቻል፡፡ ማረው እና ሰፉ (2000፣108) ቅድመ ንባብ ተግባር ያለውን ጠቀሜታ እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡

ተማሪዎች ቀድመው ስለሚዘጋጁ ወደዋናው ጽሁፍ ሲገቡ ምን መስራት እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡ ተማሪዎች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛሉ፡፡ ተማሪዎች ጽሁፉን እንዴት እንደሚያነቡ የሚያመለክቱ በመሆናቸው ለራሳቸው የንባብ ስራ ኃላፊነት እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ያጎለብታሉ፡፡

ከሚነበበው ጽሁፍ ምን እንደሚጠበቅ በማመልከት የጽሁፉን የመነበብ ፍላጎት ይጨምራል፡፡ ቀድመው የገመቱትን ወይም የሚጠብቁትን ከሚያነቡት ነገር ጋር እያነጻጸሩ እንዲያነቡ ያግዛል፡፡ በሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ ችግር ሲያጋጥም እንዴት መፍታት እንደሚቻል መንገድ ያመላክታል፡፡ ቋንቋውን በጥልቀት የመማር ፍላጎት ይጨምራል፡፡

### 2.6.2 የንባብ ጊዜ ተግባራት

ይህ ተግባር ለማስተማሪያነት የቀረበውን ንባብ የሚያነቡበት ነው፡፡ መምህሩም ተማሪዎቹ ንባቡን ተነሳስተው እንዲያነቡ የራሱ ጉልህ ድራሻ ማበርከት አለበት፡፡

ተማሪዎቹ በዚህ ደረጃ ከራሳቸው የቀደመ እውቀት በመነሳት የጽሁፉን መልዕክት ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉበት ነው፡፡ የኔሰው (1990፤22) የዚህን የንባብ ደረጃ ዓላማ ‹‹ጸሃፊዎች ለምን እንደጻፉት ለማስገንዘብ እንዲሁም አወቃቀሩንና መልዕክቱን ተማሪዎቹ ተረድተው እንዲገልጹ ማድረግ ነው›› ብለዋል፡፡ Wallace (1992) እና Greenwood (1987) እንደገለጹትም መምህራን በዚህ ተግባር ጊዜ ተማሪዎችን በማነቃቃት እና አንብበው ስላነበቡት ነገር በንባቡ ውስጥ ካሉ እንዲመለከቷቸውና ፍቻቸውን ከአገባቡ እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ ቀደም ብለው የገመቱትን ሃሳብ ከቅንጫቢው ከሚያገኙት ሃሳብ አንጻር ማሻሻል፣ በየአንቀጹ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ የሆነ ሃሳብ የትኛው እንደሆነ መለየት፣ ግራ የገባቸውን እያጣሩ መሄድ፣ በየመሃሉ ቆም እያሉ ከሚያነቡት ውስጥ የሚያገኙትን መረጃ ተጠያቂነት መመርመር፣ ከንባባቸው የሚያገኙትን መረጃ በመጠቀም ምስል በህሊናቸው መቅረጽ፣ ማጠቃለል፣ ንባባቸውን ሲያጠናቅቁ በትክክል ያልተረዱት ሃሳብ ካለ ወደኋላ ተመልሰው ዝርዝር ሃሳባቸውን መመርመር እና ያገኙትን ዋና ሃሳብ በወረቀት ላይ ወይም በህሊናቸው መመዝገብ የሚሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው በድሉ (2007፤50-51) ያብራራሉ፡፡

ከዚህ የምንረዳው ደግሞ በጊዜ ንባብ ተግባር ጊዜ ተማሪዎች ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ንባቡን እንዲያነቡና ወደ ድህረ ንባብ ተግባራት መሄድ ሳይሆን እያነበቡ በርካታ ተግባራትን ማከናዎን እንዳለባቸው ማሳወቅ ከመምህራን የሚጠበቅ መሆኑንና ተማሪዎችም ተግባራቱን መተግበር እንደሚገባቸው ነው፡፡

ማረው እና ሰፉ (2008፤108) በንባብ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መረዳት አለመረዳታቸውን ለማወቅ እንደሚረዱ እና በንባባቸው ውጤታማ ካልሆኑ ድክመታቸውንም አሻሽለው ትክክለኛውን ብልሀት እንዲከተሉ እንደሚያደርጉ በሚከተለው መልኩ ይገልጻሉ፡፡

በንባብ ጊዜ የሚሰራው ስራ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች መሆን አለበት፡፡ ይህንንም በጥያቄዎች አማካኝነት እውን ማድረግ ይቻላል፡፡ ጥያቄዎቹ ለተማሪዎቹ መርጠው እንዲያነቡ የሚያግዙ ሲሆን ለመምህራንም ተማሪዎቹ የሚያነቡትን ነገር በምን ያህል ደረጃ እንደተረዱት ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡ እያነበቡ እያሉም ተማሪዎቹን ብዙ ክንዋኔዎች ማሰራት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው የጊዜ ንባብ ተግባራትንና ጥያቄዎችን ማሰራት ተማሪዎች የሚያነቡትን አሃድ ትርጉም ያለው እንዲያደርጉትና ቀጣይ ምን ማንበብ እንዳለባቸው እንዲመርጡና እንዲነሳሱ ከማድረጉም በተጨማሪ ራሳቸውን እንዲፈትሹ ያግዛቸዋል፡፡

### 2.6.3 የድህረ ንባብ ተግባራት

ይህ ተግባር ተማሪዎቹ ሙሉ ንባቡን ካነበቡ በኋላ የሚከናዎን ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎች ወዲያውኑ ንባቡ እንዳለቀ መስራት አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹ ንባቡን ካነበቡ በኋላ በንባቡ ውስጥ የማያውቋቸውን ቃላት እና ሰዋስዋዊ አጠቃቀሞች በጥልቀት የሚመረምሩበት ደረጃ ነው፡፡ ‹‹በዚህ ተግባር ጊዜ ተማሪዎች ከምንባቡ ምን እንደተረዱ መጠየቅ፤ የማያውቋቸው ቃላት ካሉ እንዲያውቋቸው ማድረግ እና የጸሀፊውን ዓላማ ማስረዳት ይገባል›› (William ፣ 1984፣38)፡፡ ይሁን እንጂ በድህረ ንባብ ተግባራት ጊዜ ተማሪዎች ግራ መጋባት ሊገጥማቸውም ይችላል፡፡ እነዚህ ግራ መጋባቶች ደግሞ የሚመጡት የማያውቁት ቃል ካለ፣በጉዳዩ ላይ በቂ እውቀት ከሌላቸው፣ አረፍተ ነገሮች በጣም ረጃጅም ከሆኑ፣ ሲያነቡ ተገቢውን አትኩሮት ካልሰጡ፣ የደራሲውን ዓላማ ካልተረዱ፣ሊሆን እንደሚችል በድሉ (2007፣ 51-53) ይገልጻሉ፡፡

ችግሮቹ ከላይ ከተጠቀሱት በአንዱ ወይም በሁለቱ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን እነዚህን ችግሮች ለይቶ በማውጣት መፍትሄ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎቹም ያነበቡትን ነገር በጥልቀት እንዲያስቡ፣ ያነበቡትን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ እንዲሁም አዲስ ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ ማበረታታት አለባቸው፡፡ ማረውና ሰፉ (2000፣111-112) ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለማስወገድ ተጨማሪ ጥያቄ፣ ውይይት፣ ትወና፣ ስዕል፣ ሙዚቃና ዳንስ፣መጻፍ፣ ተግባራዊ ማድረግ እና ገሀዱን ዓለም መድረስ እንዲሁም ቅንጫቢን እንደገና መናገር በድህረ ንባብ ክንዋኔዎች ጊዜ ጠቀሜታቸው የጎላ እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡

ተጨማሪ ጥያቄ፡- ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ እንዲተነትኑ፣ እንዲተረጉሙ ወይም ያነበቧቸውን መረጃዎችና ሃሳቦች በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲያብራሩ የሚያግዙ መሆን አለባቸው፡፡

ውይይት፡- ተማሪዎች አዲስ ግንዛቤያቸውን እና እይታቸውን በጋራ ለመካፈል እንዲሁም ሃሳብን በነጻ እንዲለዋወጡ ያግዛል፡፡

ትወና፣ ስዕል፣ ሙዚቃና ዳንስ፡- በንባብ አማካኝነት  አዲስ ባገኙት ሃሳብ እና በዳራዊ እውቀታቸው መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ያግዛል፡፡

መጻፍ፡- ቀደም ሲል በሚያውቁት እና አዲስ ባገኙት ሃሳብ መካከል አንዳንድ ትስስር እንዲፈጥሩ ለማድረግ ያግዛል፡፡

ተግባራዊ ማድረግ እና ገሀዱን ዓለም መድረስ፡- በንባብ በተገኘው እና በዳራዊ እውቀት መካከል ያለውን ግንኙነት ያጠናክራሉ፡፡

ቅንጫቢን እንደገና መናገር፡- ዋናውን ሃሳብ ማውጣት እና ማጠቃለል፡፡

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ ነጥቦች ማድረጋችን ተማሪዎች ስለቅንጫቢው በጥልቀት አውቀው የድህረ ንባብ ተግባራትን በተገቢ መንገድ ማከናወን እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂላቸው እንዲጎለብት ከላይ የተዘረዘሩትን ሦስት ደረጃዎች ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ ሦስቱ የንባብ ትምህርት ደረጃዎች የተማሪዎችን የቋንቋና አካባቢያዊ እውቀት በማገናኘት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያግዛል (William፣1984) ፡፡

## 2.7. የአንብቦ መረዳት ትምህርትን የማስተማሪያ ብልሃቶች

በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን ማስተማር ከፍተኛ ጥበብን የሚሻ ነው፡፡ ምክንያቱምተማሪዎቹ ለማስተማሪያነት የቀረበውን ንባብ እንደ ዓላማና ግቡ በተነሳሽነት እና በፍላጎት እንዲያነቡት የቋንቋ መምህራን ከፍተኛ ሚና መጫወት አለባቸው፡፡ አንብቦ መረዳትንለማስተማር የሚያገለግሉ የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀም እንደምንችል በድሉ (2007) እና ማረውና ሰፋ (2000) በሰፊው አብራርተውት እናገኛለን፡፡ ብልሃቶቹም፡- ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ አንድምታና ትንበያ እንዲሁም ምሰላ እንደሆኑ ሲገልፁ ምሁራኑ የንባብ ብልሃቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ጥያቄ መጠየቅ**(questioning)፡- ተማሪዎችን ጥያቄ ስንጠይቃቸው ስለንባቡ የማወቅ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በንባቡ ዙሪያ የሚያተኩሩ ጥያቄዎችን

መጠየቅ አለብን፡፡ መምህራን ንባብን እያስነበቡ ንባባቸውን አቋርጠው እያነበቡ ምን ያስቡ እንደነበር መጠየቅ አለብን፡፡ በድሉ ሲገልፁም ተማሪዎቹ በማንበብ ላይ እያሉ የሚነበበው ቅንጫቢ ትርጉም አልሰጥ ሲል መልሶ ማንበብ፣አንድ አረፍተ ነገር ከተነበበ በኋላ የሚቀጥለው አረፍተ ነገር ምን ሊል እንደሚችል መገመት፣ እየተነበበ ያለው ቅንጫቢ የሚፈጥረውን ምስል በህሊና መሳል፣ አዲስ ርዕስ ሲያጋጥም በቀደመው ርዕስ ስር የተነበበውን ማጠቃለል፣ፀሀፊው ምን ለማለት እንደፈለገ መደምደሚያ ላይ መድረስ፣ከሚያከናውኗቸው ድርጊቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ አስቀምጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ከቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች እያነበቡ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ከሆነ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ክሂል ይኖራቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Block (1993) እና በድሉ (2007) እንደገለፁት ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ቅንጫቢውን ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እንዲያስማሙ እና እንዲያነቡ ያግዛል፡፡ ጥሩ አንባቢ ለመሆንም ምን አውቃለሁ? ምን ለማወቅ እፈልጋለሁ? እና ምን አወቅሁ? የሚሉ ጥያቄዎችንም መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡

Zeynali et al. (2015) በበኩላቸው ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃት ስለትክክለኛነት ጥያቄ መጠየቅ፣ ብዥታ ላለበት ሀሳብ ማብራሪያ መጠየቅና የቋንቋ ተግባራት በሚከዎኑበት ጊዜ እገዛ መጠየቅ የሚሉ ስልቶች ታላሚ ቋንቋውን እንዲገነዘቡ የሚያስችሉ ብልሃቶች ናቸው በማለት ገልፀውታል፡፡ ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን መምህራንን ወይም ሌሎች አፊ- ፊት ተናጋሪዎችን ደግመው እንዲነግሯቸው (repitition)፣ በራሳቸው አባባል እንዲገልፁላቸው (paraphrasing)፣ እንዲያብራሩላቸው (explanation) እና ምሰላ እንዲሰጧቸው (example) መጠየቅ ነው፡፡ በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም O.Malley & Chamot (1990) ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን የማብራሪያ ጥያቄ መጠየቅ ወይም የማረጋገጫ ጥያቄ መጠየቅ የሚሉትን ዘዴዎች ሲሆን ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ተግባራት በራስ አባባል መግለፅ፣ ስለጉዳዩ ምሰላ መጠየቅ፣ ራስን ጥያቄዎች መጠየቅ ናቸው ይላሉ፡፡ Oxoford (1990) ደግሞ ግልፅነት ጥያቄ በመጠየቅና የማስተካከያ ጥያቄ በመጠየቅ የብልሃቱ መተግበሪያዎች ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

**ማብራራትና መተርጎም** (explaining and interpreting) ተማሪዎች ያነበቡትን ንባብ እንዲያብራሩና እንዲተረጉሙ ማድረግ አንብቦ መረዳት ችሎታቸው ይጨምራል፡፡"ተማሪዎች ዝርዝር ጉዳዮችን ማስታወሳቸው ማን? መቼ? እንዴት? የት? እና ለምን? ከዋናው ሀሳብ ጭብጥ እንዲገናኝ ለማወቅ ይረዳል" በድሉ (2007) ፡፡ መምህራንም በዚህ ዘዴ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት እውቀት እንዲዳብር ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ፅሁፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመፃፍ የሚገልፁበት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

**ማጠቃለያ** (summarizaing)፡- ተማሪዎች ሲያነቡ ማጠቃለያ እየሰጡ ማንበባቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ሲያነቡ ማጠቃለያ እየሰጡ እንዲሄዱ የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች ማወቅ እንደሚገባቸውና ብልሃቶቹም ድግግሞሽን ማስወገድ (በሚያነቡበት ወቅት ከዓረፍተ ነገር ጀምሮ ያለውን ሀሳብ ለመረዳት በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ አንድ ዓይነት ሀሳብ የሚገልፁ ቃላት እና ሃረጋትን ማስወገድ) ሃሳብን በጥቂት ቃላት እንደገና መግለፅ፣ ተመሳሳይ ሃሳቦችን ማቀናጀት፣ አጠቃላይ ቃላትን መጠቀም (ከሞላ ጎደል፣ ዋናው ነጥብ፣ በድምሩ ለማጠቃለል) እና ዋናውን ጭብጥ የማይደግፉ ሃሳቦችን ማስወገድ እንደሆነ በድሉ2007) በሰፊው አብራርተውት እናገኛለን፡፡

**አንድምታ እና ትንበያ** (inferring and predicating) ፡-ይህን የማስተማሪያ ብልሃት በተመለከተ Block (1997) መተንበይ አንድን ፅሁፍ አንብቦ የሚገኘውን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቀምበት ልዩ ስልት ነው፡፡ እንዲሁም Barrs(2003) መተንበይን በሚመለከት የሰጡት ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንድን ፅሁፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገፀባህርያትን ማንነት፣ድርጊት፣ሴራ በመረዳት ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡

አንድምታ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ለማዳበር የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ በድሉ (2007) Weaver እና kinstch (1991) ን በመጥቀስ ገልፀዋል፡፡

አንድምታ ከንባብ የተገኘን መረጃ በመመርኮዝ መደምደሚያ መስጠትን ሲመለከት ትንበያተማሪዎች ንባቡን እያነበቡ ወደ ፊት የሚፈጠረው ነገር ምን ሊሆን

እንደሚችል መገመት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚሰጡት አንድምታ እና ትንበያ የተሳሳተ ሊሆን ስለሚችል መምህራን ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡ የተሳሳተ አንድምታ ከተጠቀሙ ከዋናው ሀሳብ ሊወጡ ይችላሉ፡፡ "የተሳሳተ አንድምታ መጠቀም የቅንጫቢውን ትክክለኛ ሀሳብ ለመረዳት እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህ እንዳይሆን ተማሪዎች ለሚደርሱበት አንድምታ እና ለሚያደርጉት ትንበያ ምክንያታቸውን እንዲገልፁ በማድረግ የአንድምታና የትንበያ ችሎታቸውን ማዳበር ያሻል" በማለት በድሉ (2007) ገልፀዋል፡፡

**ምሰላ** (imaging)፡- ተማሪዎች ስለሚያነቡት ነገር ምስል እየፈጠሩ እንዲያነቡ ማድረግ ሲሆን መምህራን ተማሪዎቻቸውን ምሰላ ማለማመድ አለባቸው፡፡ ምሰላን ለማለማመድም ተማሪዎች እያነበቡ ከንባብ የሚያገኙትን መረጃ በአዕምሯቸው ምስል መፍጠር እንዳለባቸው መግለፅ፣ አንባቢው ከተናገሩ በኋላ በቅንጫቢው ላይ ሌላ ሀሳብ በመጨመር በአእምሯቸው የተጨመረውን ለውጥ እንዲናገሩ ማድረግ እንዲሁም ተማሪዎች የሚያነቡትን ቅንጫቢ ዋና ሀሳብ በማነፃፀር እንዲገልፁ ማድረግ ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ በድሉ(2007) ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ስለብልሃቶች ምንነት ከቀረቡት መረጃዎች ማጠቃለል የሚቻለው ብልሃቶች የመማር ችግርን ለመፍታት ወይም መማርን ለማቀላጠፍ የምንጠቀምባቸው ዝርዝር ዘዴዎች ናቸው ቢባልም፣ ስለብልሃቶች ምንነት በጥልቀት ለመረዳት ደግሞ መለያ ባህሪያቸውን መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

እንደ Oxoford (1990) ገለፃ ደግሞ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ምክንያታዊ መሆን፣ መተንተን መረጃ መቀበል እና ማቀበል ግርፍ እና አሰሳ ንባብን በመጠቀም ዋና ሀሳቡን በፍጥነት ማግኘት እና ቃላትን ማመላከት ወይም መዘርዘር ፣ለግብዓት እና ውጤት መዋቅር መፍጠር (ከሰፊ ንባብ ውስጥ ማጠቃለያ መያዝ ወይም ማጠቃለል፣ ማስታወሻ መያዝ፣ መተንበይ፣ዋና ዋና ሀሳቦችን ማውጣት፣ የነገሮችን አንድነት እና ልዩነት በመለየት፣ ሀሳቦችን እንደገና ማደራጀትን ያካትታል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

**ደጋግሞ የማንበብ ብሃልት**፡- ደጋግሞ የማንበብ ብልሃት አንድን ምንባብ ወይም ፅሁፍ ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት ከአንድ በላይ ደጋግሞ ማንበብ ማለት ሲሆን፣ ፅሁፎችን ለማንበብ ብዙ ጊዜ ተመራጭ የሆነ ብልሃት ነው፡፡ ስለሆነም ለተለያዩ

አላማዎች ለምሳሌ የፅሁፉን ዋና ሀሳብ አቅጣጫ ለማግኘት፣ለመተንበይ ፣ በጥልቀት ለማንበብ ፣ ጥያቄዎችን ለማውጣትና ለመሳሰሉት እንደሚያገለግል Oxoford (1990) ያስረዳሉ፡፡ ምሁሩ አክለውምይህንን ብልሃት በንባብ ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ማስታወሻ እንዲወስዱ እና በፅሁፉ ላይ ሂስ እንዲሰጡ እንደሚያስችላቸው ያስረዳሉ፡፡

በአንድ ቋንቋ ተግባራት ውስጥ ትምህርቱን በተገቢ ሁኔታ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ቃላትና ሀረጋት የሚደጋገሙበት ሁኔታ ወይም አጠቃላይ የመማር ክንውኑ ደግሞ መሰራት የመለማመድ ብልሃት ነው O.Malley and chamot (1995) በተመሳሳይ Ratana (2014) ደግሞ የማንበብ ብልሃት በንባብ ጊዜ ተግባራዊ የሚሆነው አንድን ንባብ ከአንድ ጊዜ በላይ ሲነበብ እንደሆነ ይገልፀሉ፡፡

ማረው (1998) እንደነ አርም ብሩስታርና ኦስቦርንን ጠቅሰው የማንበብ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶችን በተመለከተ እንደገለፁት አንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በቀጥታ በማስተማር ክሂሉን በማጎልበት ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ የማሳደጊያ ዘዴዎቹም፡-

**እንደገና መናገር፡-** ተማሪዎች ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን ታሪክ መልሰው እንደገና በራሳቸው እንዲያዋቅሩ እድል ቢሰጣቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንደሚጎለብት ይታመናል፡፡

**መገመት፡-** በፅሁፉ ያለውን መነሻ በማድረግ ወደፊት የሚመጣውን መተንበይ ወይም መገመት ይቻላል በዚህ ጊዜ አንባቢዎች በሁለት መንገድ በሚያነቡት ፅሁፍ ዙሪያ ያለውን መልዕክት መገመት ይችላሉ ይኸውም በሚነበበው ፅሁፍ የሃሳብ ዝምድና አማካኝነት መገመት መቻል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ የገፀ ባህሪ ታሪክ መነሻ በማድረግ መገመት መቻል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የገሃዱ አለም እውቀት መነሻ በማድረግ በፅሁፉ ውስጥ ያልተባለውን ማውጣት መቻል ነው፡፡ ለአብነት በፅሁፉ ያልተሟሉ ወይም የተዘለሉ ዝርዝር ሃሳቦችን መሙላትን፣ ከተባለው ነገር በላይ መግለፅን ወይም ማብራራትን፣ ወደፊት ወይም ቀጥሎ ምን እንደሚመጣ መገመትን ያካትታል፡፡

**ዋናውን ሀሳብ ማውጣት** ፡-የፅሁፉን አወቃቀር ወይም አደረጃጀት ማወቅ በውስጡ የትኛው ሀሳብ በጣም አስፈላጊ የትኛው ደግሞ አላስፈላጊ መሆኑን ለመለየት ይረዳል፡፡ ይህ ክሂል ያላቸው አንባቢዎች የሚያነቡትን ፅሁፍ አንጻራዊ ና አስፈላጊ ሀሳብ በቀላሉ ይለያሉ፡፡ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ሀሳቦችን ለመለየትም ሦስት ዘዴዎች አሏቸው፡፡ እነዚህም

ሀ) የመጀመሪያው የፅሁፉን መልዕክት ለመረዳት አጠቃላይ ዳራዊ እውቀትና የቀደመ እውቀትን ይጠቀማሉ፡፡

ለ) ሁለተኛው በፅሁፉ ውስጥ ያለውን ሀሳብ አወቃቀር ለማወቅ የቴክስት አወቃቀር ወይም አደረጃጀት እውቀታቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ይህም መላውን የፅሁፉን አወቃቀር ማለትም ዋና ዋና ርዕሶችን፣ንዑሳን ርዕሶችን፣ የክለሳና የማጠቃለያ ሀሳቦችን፣ቁልፍ ቃላትንና ሀረጋትን፣ስዕላዊ ወይም ግራፋዊ አቀራረቦችን ሁሉ ይመለከታል፡፡

ሐ) ሦስተኛው የአንባቢውን ግላዊ አስተያየት ፣እድል አላማና ሰላምን መነሻ በማድረግ በፅሁፉ የትኛው ሀሳብ የበለጠ አሰፈላጊ ወይም ጠቃሚ እንደሆነ ይለያሉ፡፡

**ማጠቃለል**፡- በፅሁፉ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በትኩረት ማለፍን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም የፅሁፉን ቢጋር ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ቢጋር በማጠቃለያው የሚካተቱትን ሀሳቦች የሚያመለክቱ ቁልፍ ቃላትን ይይዛል፡፡ መሠረታዊ የማጠቃለያ ህጎችን በመከተል ማጠቃለል ደግሞ ሌላኛው አማራጭ ሲሆን፣ህጎቹም፡- ተራ ሀሳቦችን መደገፍ፣ተደጋጋሚ ሀሳቦችን መደገፍ፣ዝርዝሮችን በጥልቅ መመሪያ መተካት፣መጭመቅ፣የየአንቀፆችን ሀይለቃል መለየት፣ሀይለ ቃል ለሌላቸው አንቀፆች ሀይለ ቃል መፃፍ የሚሉት ናቸው፡፡ ማጠቃለል ውስብስብ ሥራ በመሆኑ በሂደት በመማርና በመለማመድ ቀስ በቀስ የሚዳብር ክሂል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**ምስል መፍጠር**፡- ተማሪዎች የሚያነቡትን ፅሁፍ ምስል እየፈጠሩ መረዳት እንዲችሉ ገላጭ ፅሁፍ እያነበቡ እያሉ አንድ ዓይነት ምስል የፈጠረላቸውን ቃል ወይም ሐረግ ለይተው እንዲናገሩ እድል በመስጠት ይጠቅማል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች እንደምንረዳው የንባብ ክሂልን ለማዳበር የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በቀጥታ ማስተማር የማስተማሪያ ፅሁፎችን ትኩረት ሰጥቶ መምረጥና የተማሪዎችን የቀደመ ችሎታ ማወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው እንረዳለን፡፡

Parson (2009) የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡

**ሀሳብ ማፍለቅ** (Brain Storming)፡- ይህ ቴክኒክ በትንሽ ወይም በትልቅ ቡድን አደረጃጀት ችግር ፈቺና የፈጠራ ብቃትን የሚያሳድግ ነው፡፡ አገልግሎቱም ምንም ችሎታ የሌላቸው በነፃነት እንዲሳተፉና ሃሳብ አፍልቀው በቡድን አባላቱ ማቅረብ እንዲችሉ እድል ይሰጣል፡፡

**ድምፅን ከፍ አድርጎ በበድን ማንበብ** (Choral Reading)፡- ተማሪዎች የንባብ ፍላጎትን ለማዳበር የሚጠቅም ነው፡፡ ለዚህ የንባብ ልምድ ዝግጁ ሆነው ሲለማመዱ ንቁ ተሳታፊ ያደርጋቸዋል፡፡

**ውይይት** (Discussion)፡- አጫጭር ታሪኮች ፣ተራኪ ድርሰትና ስድንባብ ላይ የተመሠረተ የቡድን ውይይት ማድረግ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎትና ችሎታ ለማዳበር የሚጠቅም ነው፡፡

**ግራፍ ማደራጀት** (Graph Organizer)፡- ግራፍ አደረጃጀት የንባብ ብልሃት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመጠቀም ከቀረበው የንባብ ይዘት ዋና ሀሳብ ጋር በማቀናጀት በግራፍ ሃሳብን ለመግለፅ የሚያግዝ የአንብቦ መረዳት ብልሃት ነው፡፡ ግራፍ የተለያዩ መመሪያዎች አሉት፡፡ ካርታ (Map)፣ቻርት፣ፍሬም ወይም ክላስተር ናቸው፡፡ ተማሪዎች ይህንን የንባብ ብልሃት ተጠቅመው ያነበቡትን ሃሳብ በሚታይና ግልፅ በሆነ መንገድ ለማስታወስ እንዲያመች በስዕላዊ መግለጫ ማስቀመጥ እንዲችሉ የሚያደርግ ነው፡፡

**ጥያቄ** (Open-ended questions):- ግልፅ ጥያቄ የተማሪዎችን ብዙ ማሰብና ሀሳብ የማፍለቅ ክህሎትን ያሳድጋል፡፡ ተማሪዎቹም ያወቁትንና የገመቱትን በሚፈልጉት ልክ የመግለፅ እድል እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ በሁሉም የእድሜ ደረጃ ላሉ ልጆች የሚያገለግል ነው፡

**በጥንድ ንባብ** (Pair reading)፡- ሁለት ተማሪዎች በጋራ የሚያነቡበት የንባብ ብልሃት ሲሆን የንባብ ፍጥነትንና በብቃት ማንበብ እንዲችሉ የሚያፎካክር ነው፡፡ ለዚህ የሚሆን ምንባብ ያልተንዛዛና አጭር መሆን አለበት ተማሪዎችን እየሳበና እየማረከ በፍጥነትና በትክክል እንዲያነቡ የሚገፋፋ የንባብ ብልሃት ነው፡፡

**ቅድመ ግምት** (Preview)፡- ይህ የንባብ ብልሃት ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ስለ ምንባቡ የሚገምቱበት የንባብ ብልሃት ነው፡፡

**መተንበይ** (predicate) ፡- ይህ ብልሃት ተማሪዎች ወደ ፊት የሚያነቡት ምንባብ ስለምን እንደሆነ ምን ይዘት እንዳለበትና ለማህበራዊ አገልግሎት የሚኖረውን ፋይዳ የሚገምቱበት ወይም የሚተነብዩበት ነው፡፡

**ጥያቄና መልስ** (questions and answer)፡- ጥያቄና መልስ የንባብ ብልሃት የተማሪዎቹን አንብቦ መረዳት ክህሎት የሚያዳብርና ያነበቡትን ይዘት እንዲገነዘቡና ለንባብ ጥያቄ ማብራሪያ እንዲሰጡ እድል ይሰጣል፡፡ መምህራን ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ለተማሪዎች በማቅረብ ከተማሪዎች የምንባቡን ግብረ-መልስ የሚያገኙበትና የሚያረጋግጡበት ብልሃት ነው፡፡ ይህ ብልሃት የምንባቡን ሀሳብ የመግለፅ፣የማመዛዘን፣የመተንተንና ማጠቃለያ የመስጠትን ብልሃት የሚያዳብር ነው፡፡

**መልሶ መንገር** (Reteling)፡-አንድ ንባብ ከተነበበ በኋላ ሀሳቡን መልሶ ለሌሎች መንገር ወይም ማቅረብን የሚመለከት ብልሃት ነው፡፡ ይህ ብልሃት የንባብን ገጸ ባህሪያት፣ ጭብጡን፣ ትልሙን፣ ታሪኩን፣ ቦታ ጊዜና ሂደት ለመግለፅ የሚያደርግ ነው፡፡ ህፃናት አንድን ተረት ካነበቡ በኋላ ለሌሎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚተርኩበትና የሚገልፁበት ብልሃት ነው፡፡ ስለሆነም ብዙውን ጊዜ ይደሰቱበታል፡፡

**ሚና ጨዋታ** (Role play)፡- ሚና ጨዋታ በሞዴሊንግ መልክ ለማስተማር የሚያገለግል ብልሃት ነው፡፡ ይህን ሞዴል ተጠቅሞ ለመማርም ሆነ ለማስተማር አንድን የንባብ ሂደት ደጋግሞ በማንበብ ጭብጡን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ሚና ጨዋታ ክንዋኔ ተኮር በመሆኑ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ገፀ-ባህሪያት ሚና ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

**ማደማደሚያ ብልሃት** (sumary)፡- አንድን ንባብ ካነበቡ በኋላ ዋና ዋና ነጥቦችን በመለየት አጠቃሎ በአጭር አገላለፅ የመግለፅ ብልሃት ነው፡፡ አጠቃሎ ብልሃት የተመረጡ ሀሳቦችን በመውሰድ ወይም ዋናውን ሀሳብ ሳይለቅ ስለምንባቡ የራስን ሀሳብ የመፃፍ ወይም የመናገር ብልሃት ነው፡፡

Silver (1989) የማንበብ ችሎታ አንባቢዎች የፅሁፉን ትርጉም እንዲሰጡ ብቻ ሳይሆን ጠለቅ ብለው ዘልቀው እንዲገቡና የፀሐፊውን ሀሳብ እንዲፈቱ ያስችላቸዋል፡፡ ጎበዝ አንባቢ ለመሆን ተማሪዎች ፅሁፎችን ለመረዳት እንደ መሳሪያ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን ብልሃቶች ማግኘት አለባቸው፡፡ ተማሪዎችን ለመርዳት መምህራን ለእያንዳንዳቸው እነዚህ ችሎታዎች በተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው፡፡ በማለት ብልሃቶቹንም እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡-

**ቃላትን በአውዱ መረዳት** ፡- ቃላት ወይም ሐረጎች በዓረፍተ ነገር ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ፣አንድን ቃል በዓረፍተ ነገር ውስጥ ማስቀመጥ ወይም በዙሪያው ያሉትን ቃላቶች መመልከት ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡ ለዚህም ለተማሪዎች ስለአንድ ቃል ወይም ሐረግ ትርጉም እንዲያስቡ ለመርዳት ዘይቤያዊ አቀራረብን መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡

**መረጃን መፈለግ፡-** ስለ አንድ ቁልፍ ቃል የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት የፅሁፉን የተወሰኑ ቦታዎች ማንበብና እንደገና ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ክህሎት ለማግኘት፣ መምህራን ቁልፍ ቃላትን ለማግኘት ፅሁፉን በመቃኘት ላይ መመሪያ ሲሰጡ እና ፅሁፉን በጥንቃቄ ማንበብ አስፈላጊ መሆኑን እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አስፈላጊ እና ደጋፊ መረጃዎችን እና ዝርዝሮችን ለማግኘት ማጉላት ይችላል፡፡

**ዋናውን ሀሳብ መለየት፡-** ተማሪዎች የአንድን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ መለየት ከቻሉ የመረዳት እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ ዋናው ሀሳብ በአንቀፆቹ ውስጥ የተገለፁትን ሀሳቦች ያገናኛል እና ለፅሁፉ ወጥነት ይሰጣል፡፡ መምህራን የነጠላ አንቀፆችን ዋና ሀሳቦች በመመልከት ይህን ሂደት መጀመር እና ከዚያ ማስፋት ይችላሉ፡፡

**ቅደም ተከተል፡-** ይህ ክህሎት በክስተቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመለየት አንዳንድ ጊዜ የጊዜ ጠቋሚታዎችን እና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም የተከሰቱትን

ቅደም ተከተሎች በቅደም ተከተል ማስቀመጥ መቻል ነው፡፡ ከጥያቄው ቅደም ተከተል የሚያስፈልጋቸውን ክንውኖች በመወሰን፣በፅሁፉ ውስጥ ማግኘት እና ቃላትን በመፈለግ፣ተማሪዎች የክስተቶችን ቅደም ተከተል ማወቅ ፅሁፉን ለመረዳት ወሳኝ ነገር መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡

**ተመሳሳይነቶችን እና ልዩነቶችን መፈለግ፡-** በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች ማነፃፀር እና ማወዳደር ለአንባቢያን ግንዛቤ ይረዳል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች እንዲለማመዱና እንዲቆጣጠሩት የሚያስፈልጋቸው ቁልፍ የመረዳት ችሎታ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ አንዳንድ መንገዶች፣አንዳንድ ሰዎች ቦታዎች እና ክስተቶች የሚያመሳስሏቸውን ወይም እንዴት እንደሚለያዩ ለማወቅ መረጃን መከፋፈልን ያጠቃልላል፡፡

**መተንበይ፡-** ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ሊለማመዱቸው ከሚችሉት አስቸጋሪ ችሎታዎች አንዱ ነው፡፡ በመሰረቱ በፅሁፉ ውስጥ በግልፅ ያልተገለፁ ውጤቶችን ለመተንበይ ከፅሁፍ መረጃ መጠቀምን ያካትታል፡፡ ከተጠቆሙት የማስተማር ግንዛቤ ስልቶች አንዱ ተማሪዎች በፅሁፉ ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ እና ሊገኙ የሚችሉ ውጤቶችን ለመወሰን እና ከዚያም ትንበያዎችን እንዲገመግሙ ማስተማር ነው፡፡

**ማደማደሚያ፡-** ይህ ክህሎት ፅሁፉ የሚያቀርበውን መረጃ ሁሉ መሰብሰብ፣ፍርዶችን መስጠት እና በፅሁፉ ውስጥ በተገለፁት እውነታዎችና ዝርዝሮች ላይ በመመስረት ማጠቃለያ ላይ መድረስ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በፅሁፉ ውስጥ ተገቢውን መረጃ በማግኘታቸው ለአንድ የተወሰነ መደምደሚያ ማስረጃ መፈለግ እንዲችሉ ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡

**ማጠቃለያ፡-** ለዚህ ክህሎት ተማሪዎች ጠቃሚ መረጃዎችን በማገናኘት እና ዋና ዋና ነጥቦቹን በመለየት ፅሁፉን ያጠቃልላሉ፡፡ ይህንን በተሳካ ሁኔታ ለማድረግ ተማሪዎች በመጀመሪያ በመልሳቸው ውስጥ የሚፈለገውን ቅርፅ መረዳት አለባቸው የአንድ ቃል መልስ ነው ብለው እንዲይዙና የሚፈለገውን መረጃ እንዴት እንደሚያወጡ መመሪያ መስጠት ተማሪዎች ይህን ብልሃት እንዲያገኙ መርዳት ይችላል፡፡

**እውነታን መለየት፡-** የዚህ ብልሃት ትኩረት ተማሪዎች እውነት ነው ብለው የሚያምኑትን ለመወሰን በፅሁፍ እና በምስል የተደገፉ መረጃዎችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በማስተማር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

**መንስኤ እና ውጤት፡-** ይህ ብልሃት መንስኤው ወደ ውጤቱ እንደሚመራ እና የተገናኙ መሆናቸውን በመረዳት ላይ ነው፡፡ ይህ ቀላል ቢመስልም ጥቂት የመረዳት ስልቶችን ማስተማር ተማሪዎቹን ሊረዳቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎቹ በተለያዩ የፅሁፍ ዓይነቶች ውስጥ እንዲያልፉ እና የምክንያትና የውጤት ሀረጎችን እንዲያጣምሩ ያደርጋል፡፡

**እውነታ ወይም አስተያየት፡-** ተማሪዎች ወሳኝ አንባቢ ለመሆን በሀቅና በአስተያየት መካከል ያለውን ልዩነት መለየት መቻል አለባቸው፡፡ ይህ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት መረዳትን እያንዳንዱን በፅሁፉ ውስጥ መለየትና አንዱን ከሌላው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማብራራትን ይጠይቃል፡፡

**አመለካከትና ዓላማ፡-** ይህ ነጥብ እያንዳንዱ ፅሁፍ በፀሐፊ የተፃፈ አላማን በማሰብና አመለካከታቸው ስለ አንድ ርዕስ ጉዳይ ያለውን አስተያየት ነው፡፡ ለዚህ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች የተፃፈውን መመርመር፣ይዘቱን መረዳት እና ደራሲው ፅሁፉን ለመፃፍ ለምን እንዳሰበ መለየት መቻል አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን ለማስተማር ከላይ ያሉትን ብልሃቶች መጠቀም የምንችል ሲሆን እንደ ማረው እና ሰፉ (2000) አገላለፅ እነዚህን ለመተግበር የረጅም ጊዜ ልምምድ የሚያስፈልግ ቢሆንም ተማሪዎች በየትኛውም የክፍል ደረጃ ላይ ቢሆኑ ሊማሩባቸው እና ሊለማመዷቸው ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ Gunining (2006) ገለፃ አንብቦ መረዳት ብልሃት አንድ ምንባብ በምን መልኩ አንብቦ መረዳት እንደሚቻል ከማመላከታቸውም ባሻገር የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እንዳሉ አስገንዝበዋል፡፡ እነዚህ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አራት ሲሆኑ የመጀመሪያው ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚሰጡ፣ማብራራትና ማጠቃለልን የሚጠይቁ፣ግጥምጥምነትና መመርመርን የሚጠይቁ እና አንብቦ መረዳት እና መቆጣርን የሚጠይቁ ብልሃቶች ናቸው፡፡

**ቴክኒካዊ ድጋፍን የሚሰጡ (ቅድመ ዝግጅት)፡-** በዚህ ብልሃት አንድ አንባቢ ሊያነብ በተዘጋጀው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የነበረው የቀደመ እውቀት የሚያስታውሰው ለንባብ እንዲነሳሳ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በዚህ ብልሃት ለምንባቡ ርዕሰ ጉዳይ እንግዳ ያልሆኑ ተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት በቀላሉ ለማነሳሳት ይቻላል፡፡ ለዚህ የቅድመ ዝግጅት ዋና አላማ ከዋናው የንባብ ሂደት በፊት የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎታቸው እንዲነቃቃ ለማድረግ የሚያዘጋጁ የተለያዩ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ስለሚያነቡት ፅሁፍ ትኩረት እንዲሰጡ እና የንባብ ተግባር ላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የተሻለ እንዲሆን ይረዳቸዋል፡፡

**ማብራራትና ማጠቃለልን የሚጠይቁ የንባብ ብልሃቶች** እንደ Gunining (2006) ገለፃ አንባቢ ያነበበውን ፅሁፍ መሠረት አድርጎ የቀደመ ዕውቀቱን በመጠቀም ርዕሰ ጉዳዩን በበለጠ ለማብራራት የሚጥርበት ብልሃት ነው፡፡ በዚህ ብልሃት የአንባቢው የቀደመ ዕውቀት አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለዚህ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ጥያቄዎቹ እንደ ፀሀፍቱ ገለፃ ምንባቡ የሚያስተላልፈውን መልዕክት እንዲገልፁ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ እንዲያብራሩ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲያዛምዱ እና እንዲያጠቃልሉ የሚያስችሉ ጥያቄዎች መካተት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

**ቅንጅታዊ (ግጥምጥምነት) እና መመርመርን የሚጠይቁ ብልሃቶች** ፡- እንደ Wiener (1997) ገለፃ ግጥምጥምነትን የሚጠይቁ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ዝርዝር ነጥቦችን የመምረጥና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የመመርመር ሂደት ሲሆን ይህ ብልሃት የምንባቡን ዋና መልዕክት ኃይለ ቃልን መለየት፣መረጃዎችን መመደብ፣የትኛው መረጃ የበለጠ ጠቃሚ መሆኑን መገንዘብ፣ቅደም ተከተል ማስያዝን እና መከለስን ወዘተ. ያጠቃልላል፡፡ ከገለፃው እንደምንረዳው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ መሆን ያለበት የምንባቡን ኃይለ ቃል እንዲያወጡ የሚያስችሉ ጥያቄዎች የምንባቡን መልዕክት እንዲገልፁ የሚያስችሉ እና መረጃዎችን መመደብ ወዘተ. የመሳሰሉትን የጥያቄ ዓይነቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና መልዕክቶች መርምረውና ለይተው እንዲያወጡ የሚያስችሉ ጥያቄዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

**እውነታዎችን፣እንድምታዎችንና አስተያየቶችን መለየት፡-** እንደ Spears (2006) ገለፃ እውነታዎችን፣እንድምታዎችንና አስተያየቶችን መለየት የጥሩ አንባቢ አንዱ መለኪያ ሲሆን በሚነበበው ፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ ሀሳቦችን እውነታነት ወይም እንድምታነት ወይም አስተያየትነት መለየና አስተያየቶችን ከተለያየ አቅጣጫ ከቀደመ እውቀት ከነባራዊ እውነታዎች ጋር እያገናዘቡ መቀበል ወይም መቃወም የመቻሉ ደረጃ ከፍ ማለት ነው፡፡ እውነታ የሚባለውም ሲረጋገጥ ወይም ሲለካ ወይም ሊመሳከር የሚችል መረጃ ነው፡፡ በሌላ በኩል አስተያየት ከእውነታ የሚመነጭ ሆኖ ለማረጋገጥ የሚያስቸግር ሃሳብ ወይም መረጃ ነው፡፡ ከሚታወቀው የማይታወቀውን ማወቅ ወይም መረዳት መቻል ነው፡፡ ለምሳሌ ባህር ዛፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው አውስትራሊያ ውስጥ ነው የሚለው ሀሳብ እውነታ የታወቀ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ እውነታ በመነሳት "አውስትራሊያ ለባህር ዛፍ ተክል የሚስማማ ቦታ ያለበት ሀገር ይመስላል"፣ብሎ መረዳት በእንድምታ የሚረዱት ሀሳብ ወይም አስተያየት ነው፡፡ እንዲህ ያለ ብልሃት ሊዳብር የሚችለው በትምህርት ቤት፣ በትምህርት በልምምድ ሲደገፍ በመሆኑ በመልመጃዎች ውስጥ ሊካተት ይገባዋል፡፡

**መተንበይ (Predicting):-** እንደ (Kuta 2008 ፣ Spears 2006፣ Nuttall 1996) ገለፃ ትንበያ አንድ አንባቢ ከሚያነበው ፅሁፍ ጋር መስተጋብር የሚፈጥርበት አንድ መንገድ ነው፡፡ ትንበያ ማለትም አንድ አንባቢ እያነበበ ያለው ፅሁፍ ቀጥሎ ምን ምን ጉዳዮችን ሊያነሳ እንደሚችል ማሰብ ወይም መገመት ነው፡፡ በሌላ አማርኛ ትንበያ ማለት ለማንበብ የተመረጠውን ፅሁፍ ርዕስ በማየት ፅሁፉ ስለምን ሊገልፅ እንደሚችል እንዲሁም የፅሁፉን የተወሰነ ክፍል በማንበብ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን እየገመቱ (እየተነበዩ) የማንበብ ሂደት ነው፡፡

Ringe (1989, 50)"ትንበያ አንባቢዎች አስቀድመው በሚገምቱት መሰረት ግምታቸውን ለማረጋገጥ ሲያነቡ ልዩ ትኩረት በመስጠት ማንበብ ያለባቸውን መለየት እንዳለባቸው ለመጠቆም መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

ተማሪዎች ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ወይም መልዕክት ለመረዳት በሚያደርጉት ጥረት ለትንበያ የሚረዳቸው ቀዳሚ እውቀት ነው፡፡ ቀዳሚ እውቀታቸውም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

እነሱም፡-

- በቋንቋው የቀረበውን መልዕክት ለመረዳት ያላቸው የቋንቋ ችሎታ፣
- የምንባቡን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ የሚኖራቸው ቀደምት እውቀት፣ የምንባቡ የቋንቋ አጠቃቀምና አቀራረብ፣
- የቋንቋው ስርዓተ ነጥቦች አገባብ፣
- በቋንቋው ውስጥ የሚገኙትን የዲስኩር አመልካቾች አጠቃቀም፣

የምንባቡን ሀሳብ ለማጉላት ወይም ለማብራራት ተብሎ የቀረቡ ደጋፊ ፍንጮች

ለምሳሌ፡- እንደ ፅሁፍ፣ስዕል፣ሰንጠረዥ፣ንዑሳን አርዕስቶችን የሚመለከትና ከምንባቡ ገለፃ ጋር የማዛመድ ችሎታዎች ናቸው (Brawn 1994፣ Grabel 1991፣ Nuttall 1996)

እንደ Nuttall (1996) ገለፃ ትንበያ ለትምህርት የቀረበውንም ሆነ በተማሪዎች ምርጫ የሚነበብን ምንባብ ለመረዳት መሳሪያና የግንዛቤያቸውም መልዕክት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ በቅድሚያ ያነበቡትን፣ያዩትን ምንባብ ክፍል ለመረዳት ከቻሉ ቀጥሎ የሚባለውን ለመለየት ይችላሉ ለማለት ነው፡፡ የመልዕክቱ ትንበያ የሚካሄደው ከተማሪዎቹ ተዛማጅ እውቀት በመነሳት ስለሆነ አዲሱን መልዕክት ለመረዳት ለማለዘብ የተሻለ አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ምሁራኑ አክለው ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ከብያኔው መረዳት የሚቻለው አንብቦ መረዳት መልመጃ ጥያቄዎች ሲዘጋጅ ተማሪዎች ቀጥተኛ ጥያቄዎችን ብቻ ሳይሆን መመርመርን የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያግዙ ብልሃቶችን በመጠቀም እንደ ትንበያ፣ ከአውድ መረዳት ከመረጃ በመነሳት ያልተገለፀውን መረዳት፣ ከእውነታ በመነሳት አስተያየት መስጠት ከላይ የተገለፁ ብልሃቶችን መጠቀም ተገቢነት ያለው ነው፡፡

## 2.8. የንባብ ትምህርትን ለመተግበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የመጠቀም ሚና

የንባብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር የቋንቋ መምህራን ሚና ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ አሳታፊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን መከተል ይገባል፡፡ በአሳታፊ የማስተማር ዘዴ የመምህራን ሚና ቀስቃሽነትና አነሳሽነት ነው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ተግባር በንቁ ሁኔታ እንዲሰሩና እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ የሚያነቡት ለምን እንደሆነ ከማስታወቅ ጀምሮ የትኛውን ተግባር በምን ዓይነት የንባብ ስልት ማንበብ እንዳለባቸው ፍንጭ መስጠትና ማነሳሳት አለባቸው፡፡ ይህን ሀሳብ አስመልክቶ ይታያል (2003) "ስለ ንባብ ትምህርት ሂደት የጠለቀ ግንዛቤ ከኖረን ለተማሪዎች ጊዜያዊና የወደፊት ፍላጎት ተገቢ የሆነ የንባብ ትምህርት ለመተግበር ይቻላል" በማለት ገልፀዋል፡፡ ማንኛውም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመምህሩ ብቻ የሚሰሩ ሳይሆኑ በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚታገዙ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የመምህራን ሚና ተማሪዎቹን መምራትና እንዲሰሩ ማነሳሳት ሊሆን ይገባል፡፡ ተማሪዎቹም በመምህራቸው የሚቀርቡላቸውን መልመጃዎችና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀጥተኛ ተቀባይ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ለሚሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነትን የሚወስዱ ማድረግ ትግበራውን በሚገባ እንዲያከናውኑት ያግዛል በማለት ይታያል (2003) ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ አንድ መምህር በክፍል ውስጥ ጥሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃት ትምህርትን ለመተግበር ስለሚያስተምረው ትምህርት ርዕስ በቂ ዕውቀት ያለው እንዲሁም በራሱ የሚተማመን መሆን አለበት፡፡ ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ጠቃሚ የሚሆኑ ግብዓቶችን አሟልቶ መገኘትም ይኖርበታል፡፡ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣የተማሪዎችን ማንነት መረዳትና ከተማሪዎቹ ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት መፍጠርም ከቋንቋ መምህራን የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ በኃሰው (2003) ይገላፃሉ፡፡

## 2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም በዚህ ርዕስ ስር የሚዳሰሱት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ዝምድና ያላቸውን የአገር ውስጥ ቀደምት የጥናት ስራዎች ይሆናል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸውን በሚከተለው መልኩ በማደራጀት ተመሳስሎና ልዩነታቸውን በመረጃ አሰባሰብ በቦታ፣ በዘመን እና በትኩረት ነጥብ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከነዚህ ነጥቦች አንፃር የሚከተሉት ስራዎች ተቃኝተዋል፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች ለማየት ባደረገችው ፍተሻ የማስተርስና የዶክትሬት መሟያ ፅሁፎችን አግኝታለች፡፡ ከነሱም ውስጥ፡-

ተክላይ (2000) "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞን መፈተሽ በሚል ዓይነታዊ ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱን ያደረጉት በአክሱም አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2000 ዓ.ም ተመዝግበው ያሉ የስምንተኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን በንባብ ትምህርት ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀማቸውን የፈተሸ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያውም ምልከታ፣የፅሁፍና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ውጤቱም የተማሪዎቹ የብልሃት አጠቃቀም በቋንቋ ችሎታቸው ካገኙት ደረጃ ጋር ተጣጥሞ በማሳየት ረገድ የስምንተኛ ክፍል ተተኳሪ ተማሪዎች ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተሽለው ተገኝተዋል፤ከመምህራኑ የንባብ ብልሃት አጠቃቀም ጋር ያለው ተጣጥሞ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል የሚል ነው፡፡ የተክላይ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያና መተንተኛ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከተክላይ ጥናት ጋር የሚለየው በጥናቱ ተተኳሪዎች ይኸውም (የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ) በቋንቋ ችሎታቸው በተለያየ ደረጃ ያሉ ተማሪዎችን ብልሃት አጠቃቀም ከመምህራን ግንዛቤ ጋር ተጣጥሞ መኖር አለመኖሩን የፈተሸ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በግልናበመንግስትትምህርት ቤት የሚያስተምሩየ አማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል

ውስጥ አተገባበር በንጽጽር መፈተሽ ነው፡፡ እንዲሁም የተክላይ ጥናት በትግርኛ አፈ- ፊት ተማሪዎችን በመለየት የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን በስምንተኛ ክፍል መምህራን ላይ የተጠና ነው፡፡ ስለዚህ በተጠናበት ክልል፣የትምህርት ደረጃ በክፊል፣በአላማ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያያል፡፡

ጌታቸው (2013) የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አወዳዳሪ ጥናት በመንግስትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ማሟያነት የተሰራ ጥናት ሲሆን ዓላማውም፡- የዘጠነኛ ክፍል የአማሪኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አወዳዳሪ ጥናት ፤ በመንግስትና ግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት በሚል ጥናት ተደርጓል፡፡ ጥናቱ የተደረገው በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመንግስት ፡- በጊዮንና ፋሲል፣ በግል ፡- ሚሊኒዬም ፕሮግረስ አካዳሚ ፣ እሸት አካዳሚ፣ ባህርዳር አካዳሚ ፣ ኤደኤም አካዳሚ 2013 ዓ.ም በማስተማር ላይ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያውም ምልከታ ፣ ቃለመጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡

ውጤቱም ፡- በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ልዩነት እንዳለ የሚያሳይ ሲሆን የግል ትምህርት ቤቶች የተሻሉ እንደሆኑ አመልክቷል፡፡ የጌታቸው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በተጠኚዎች (መምህራን) ላይ መሆኑ ፤ አወዳዳሪ ጥናትን መከተሉ በመረጃ መተንተኛ ዘዴው ነው፡፡ ይህ ጥናት ከጌታቸው ጥናት የሚለየው በስምንተኛ ክፍል ላይ የተጠና መሆኑ፤ በቦታ፤በጊዜና በብልሃቶች ላይ በማተኮሩ ይለያል፡፡

በጎሰው (2003) "በአዲስ አበባ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ ነባርና ጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ማሟያነት የተሰራ ጥናት ሲሆን ዓላማውም ፡- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ነባር መምህራን እና ጀማሪ መምህራን በምን መልኩ እንደሚከናወን በንፅፅር መቃኘት በሚል ገላጭ ጥናት አድርጓል፡፡ ጥናቱ

የተደረገው በአዲስ አበባ ከተማ ቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ፣በሰቃ ሁለተኛ ደረጃ ፣ፊት አውራሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 2003 ዓ.ም በማስተማር ላይ ያሉ ነባርና ጀማሪ መምህራን የንባብ ትምህርት አሰጣጥ በንፅፅር የፈተሸ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያውም የክፍል ምልከታ፣የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ውጤቱም የነባርም ሆነ የጀማሪ መምህራን የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ደካማና መሻሻል የሚገባው እንደሆነ አመላክቷል፤ከሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች መካከል ግን ነባር መምህራን ከጀማሪ መምህራን የተሻለ የንባብ ትምህርት አሰጣጥ እንዳላቸው በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ የበኃሰው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በመምህራን ላይ መሆኑ፣በንፅፅር መሆኑ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከበኃሰው ጥናት የሚለየው በጥናቱ ተተኳሪዎች ማለትም የመምህራን የንባብ ትምህርት አሰጣጥ በነባርና ጀማሪ መምህራን በምን መልኩ እንደሚከናዎን በንፅፅር የቃኘ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በንፅፅር መቃኘት ነው፡፡ የበኃ ሰው ጥናት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ነባርና ጀማሪ መምህራን ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ስምንተኛ ክፍል በሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ላይ የተጠና ነው፡፡ ስለዚህ በትምህርት ደረጃ፣ ብልሃት ላይ አለማተኮሩ፣በአላማ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያያል፡፡

ይታያል (2003) “በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ” በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያደረገው ጥናት ነው፡፡ አጥኚው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በተመረጡ ሦስት የአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት እንዴት እንደሚተገበር፣አቀራረቡ ምን እንደሚመስል በስፋት ዳሷል፡፡ አጥኚው ካገኛቸው ውጤቶች በመነሳት የመፍትሔ ሀሳብ በመስጠት ጥናቱን አጥንቷል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የንባብ ክሂል ትምህርት መሠረት አድርጎ መጠናቱ፣በስምንተኛ ክፍል የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ ላይ ማተኮሩ ሲሆን የይታያል ጥናት በአማርኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ ላይ በማተኮሩ የዚህ ጥናት ደግሞ በግል ና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ  የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ንፅፅር ላይ ያተኮረ በመሆኑ

ከቀዳሚው ጥናት ይለያል፡፡ የይታያል ጥናት በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት እንዴት እንደሚተገበርና አቀራረቡ ምን እንደሚመስል በስፋት የዳሰሰ ሲሆን፣የዚህ ጥናት ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እንዴት እንደሚተገብሩት ንፅፅር ላይ ያተኩረ በመሆኑ ከቀዳሚው ጥናት ይለያል፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ ጊዜ፣በቦታ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት: የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ በአወዳዳሪ የምርምር ዘዴ የተካሄደ ሲሆን ለጥናቱ አስተማማኝ መረጃዎችን ለማግኘት አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ አወዳዳሪ ጥናት ሁለት እና ከዚያ በላይ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል በአንድ በተወሰነ ተለዋዋጭ ላይ ያላቸውን የባህሪ መመሳሰልና መለያየት ለማጥናት ያስችላል በማለት ያለው (2009) ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሥርም የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ ለጥናቱ ያገለገሉ የመረጃ መስብሰቢያ መሳሪያዎች አይነት እና አዘገጃጀት፣ እንዲሁም የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑባቸው ስልቶች ከዚህ ቀጥለን እያንዳንዳችውን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት የሚሳተፉ ናሙናዎች የሚመረጡበት መንገድ የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ቤት፣ የክፍል ደረጃ፣ የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ስልት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ካሉ የግልናየመንግስት ትምህት ቤቶች ውስጥ አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ከግል ሆሊሲቨየር ትምህርት ቤት ከመንግስት የብርሃን ጎሊና ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች በአመቺ ናሙና የተመረጡበት ምክንያት አጥኚዋ የምትሰራብት ክፍለ ከተማ በመሆኑ ጊዜና ገንዘብን (ወጪን) ይቆጥባል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡ ያለው (2009) አመቺ ናሙና ዘዴን (Conveience sampling) እንደገለፁት ተመራማሪው ጥናቱን በቅርበት ለማካሄድ አመቺ በሆነለት ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ምርምሩን ሲካሂድ አመቺ ናሙና ተጠቀመ  ማለት ይቻላል በማለት ገልፀዋል፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚካተቱት የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የስምንተኛ ክፍል በዓላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ብላ ስላመነች ነው፡፡ በተጨማሪም በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ማስተማሪያነትየቀረቡ መልመጃዎች በርካታ ስለሆኑ አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊው መረጃ ሊገኝባቸውይችላል ብላ ስላመነች የስምንተኛ ክፍል በዓላማ ተኮር ናሙና ተመርጧል፡፡

የዓላማ ተኮር ናሙና ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ አላማ አንፃር እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ በማለት መረጃዎችን የሚመርጥበት ዘዴ ነውበማለት ያለው (2009) ገልፀዋል፡፡

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ወ 1 ሴት 1 በድምሩ 2 ሲሆኑ ሁለቱም በጠቅላይ ናሙና ዘዴ በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ በተመሳሳይ ወ 1 ሴ 1 በድምሩ 2 ሲሆኑ እነዚህም በጠቅላይ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ በአጠቃላይ ከሁለቱም ትምህርት ቤት አራት መምህራን ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በጠቅላይ ናሙና የተመረጡበት ምክንያትም አጥኚው የጥናቱን አካላዮች ሁሉንም በጥናቱ አካቶ ምርምሩን የሚያካሂድበት ዘዴ መሆኑን ያለው (2009) ገልፀዋል፡፡

### 3.2.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤት በእያንዳንዱ ክፍል በአማካኝ 56 ተማሪዎች ከሦስቱ የመማሪያ ክፍሎች በድምሩ 168፣ በግል ትምህርት ቤት ደግሞ በእያናዳነዱ በአማካኝ 38 ተማሪዎች በሦስቱም የመማሪያ ክፍሎች 114 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡

በዚህም መሰረት ከእያንዳንዱ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ከእያንዳንዱ ክፍል (ሴክሽን) 12 ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በአጠቃላይ ከሁለቱም ትምህርት ቤት 72 ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠው በመረጃ ሰጪነት ተካተዋል፡ ፡ይህም የጥናቱን አካላይ የስም ዝርዝር በማዘጋጀትና እጣ በማውጣት የሚፈለገው የእጣ ናሙና መጠን ተመርጦ በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ያለው(2009) ይህ ዘዴ በአመዛኙ የሚያገለግለው የጥናቱ አካላይ ቁጥር አነስተኛ ሲሆን ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ የናሙና ዘዴ እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል ናሙና ሆኖ ለመመረጥ እኩል እድል አለው፤ በተጨማሪም እያንዳንዱ አባል የናሙናው አካል ሆኖ ለመመረጥ ሙሉ ለሙሉ የሚወሰነው እድል ወይም አጋጣሚ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የምርምር አይነቱን በተከተለ መልኩ የሚከናወን የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የመጀመሪያ የመረጃ ምንጭ በሆሊሴቨር ትምህርት ቤትና ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያሉ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ትኩረት በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በንፅፅር መቃኘት ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑት መምህራንና ተማሪዎች ከሚሰበሰቡት መረጃዎች በቂ እና አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት እንዲቻል ሦስት ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም ምልከታ፣የፅሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1 የክፍል ምልከታ

ከምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ቅፅ በምዕራፍ ሁለት ላይ የቀረቡትን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ ዝግ ጥያቄዎች በአጥኚዋ ተዘጋጅተው ልምድ ባላቸው መምህራንና በአማካሪ ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በዚህም መሰረት በተመረጡት በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር በንፅፅር ለመፈተሽ የሚያስችለውን መረጃ ለማግኘት ቀጥታ ምልከታ ስልትን በመከተል

ክፍል ውስጥ ተገኝቶ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሦስት ጊዜ ምልከታ ተደርጓል፡፡ ሁለቱን በፕሮግራም (ለመምህራን ተነግሮ) አንድ ጊዜ ሳይነገራቸው በድንገት በመግባት መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.3.2 የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሑፍ መጠይቁን የሚሞሉት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በቁጥር በዛ ያሉ ስለሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ሂደት ላይ ውስብስብ እና አስቸጋሪ ስለሚያደርገው ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ መረጃውን በቀላሉ ለመሰብሰብና ለመተንተን ያስችላት ዘንድ ሁሉንም ጉዳዮች የሚዳስሱ ጥያቄዎችን ተጠቅማለች፡፡ የፅሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት የተመረጠበት ዋና ምክንያት መረጃ ሰጪዎቹ ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን፣ያላቸውን አመለካከትና አስተያየት በትክክል እንዲሰጡ ያስችላል በሚል ግምት ነው፡፡

እንደ ያለው (2009) አገላለፅ የፅሁፍ መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጋር ሲነፃፀር በአጭር ጊዜ ከብዙ ተጠኚዎች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ ጊዜን፣ ገንዘብንና ጉልበትን ቆጣቢ ሲሆን የመላሾቹንም ማንነት ስለማይገልፅ መላሾች ነፃ በመሆን በድፍረት ከይሉኝታ በፀዳ መልኩ ሃሳብን መግለፅ ስለሚያስችል መላሾች አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ያበረታታል፡፡ በምርምር ሂደትም በብዛት ጥቅም ላይ ይውላል፡

የፅሁፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎቹን ዳራ የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል መምህራን የሚያከናውኑትን የማስተማር ተግባራት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የሚካተቱት ጥያቄዎች ሁሉም በ”Likert scale” በአምስት ደረጃዎች (5. በጣም ከፍተኛ፣ 4. ከፍተኛ፣ 3. መካከለኛ 2. ዝቅተኛ፣ 1 በጣም ዝቅተኛ) በሚሉ አማራጮች ቀርበዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ የተሞላው በተማሪዎች ብቻ ነው፡፡

### 3.3.3 ቃለ መጠይቅ

በቃለ መጠይቅ በአራት ክፍት ጥያቄዎች ላይ ከአራት መምህራን መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡በቃለ መጠይቁ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ዋነኛ ምክንያት በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ናሙናዎች በቁጥር ትንሽ ስለሆኑ መረጃዎቹን

ለመሰብሰብና ለመተንተን ቀላል ስለሆነና በቃለ መጠይቅ ጊዜ ተጠያቂው ያልተረዳው ነገር ቢኖር እንኳን ማብራሪያ የሚገኝበት ሰፊ ዕድል ስላለ መላሹ ትክክለኛ መልስ እንዲሰጥ ስለሚያደርግ አስተማማኝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ነው፡፡

አለም (2007) እንደገለፁት ቃለ መጠይቅ ከተጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በቃል መልስ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ በብልሃት ከተያዘና ተግባር ላይ ከዋለ ከሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያና ማጠናቀሪያ ስልቶች በተሻለ መንገድ መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ ደጋፊ መረጃዎች ለመሰብሰብ የተመረጠ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን ቃለ መጠይቁ የሚቀርበው በተመረጡት ትምህርት ቤቶች በተተኳሪው የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚያስተምሩ መምህራን ነው፡፡ ዋና ትኩረቱም የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ለመተግበር እንደ ችግር የሚያነሷቸው ጉዳዮች መኖር አለመኖራቸውን በመለየት ላይ ነው፡፡

ቃለ መጠይቁ የመምህራንን ይሁንታ በመጠየቅና ቀጠሮ በመያዝ ተከናውኗል፡፡ በምልልሱም ወቅት መምህራን የሚሰጡትን አስተያየት እንዳለ በፅሁፍ ለማስቀረት አስቸጋሪ ስለሚሆን የመምህራንን ፈቃደኝነት በመጠየቅ ምልልሱን በመቅረፀ ድምፅ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡ የተቀረፀው ድምፅ ወደ ፅሁፍ ተቀይሮ ቀርቧል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተገኘውን መረጃ ለትንታኔ እንዲረዳ አጥኚዋ ገላጭ ስታትስቲክስን ተጠቅማለች። በቁጥር መልክ የተሰበሰበውን መረጃ ገላጭ ስታትሰቲክስ (በአማካይ፣መደበኛ ልይይት“ በቲ- ቴስት ስታትሰቲክስ የመተንተኛ ስልት) በመጠቀም ተተንትኗል። በተጨማሪ በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በስርአት ከተደራጁ በኋላ በአይነታዊ የመረጃ ስልት በገለጻ መልክ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት: የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

በምዕራፍ አንድ ስር እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ መምህራን የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ከፍ ለማድረግ የአንብቦ መረዳት ብልሃትን ተጠቅመው ማስተማራቸው፣ በመማሪያ መጽሃፉ የቀረቡትን ይዘቶች እና ተግባራት ሲያስተምሩ አንብቦ የመረዳት ብልሃትን መጠቀማቸውን እና መምህራን ተማሪዎቻቸው በመማሪያ መጽሃፋቸው የቀረቡ ይዘቶችን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ እያበረታቱ ማስተማራቸውን ለመፈተሽ ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ እና ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተደራጅተው እንደሚከተለው ተተንትነዋል›፤ የጥናቱም ግኝት ተብራረቷል፡፡

## 4.1 የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ

*ሠንጠረዠ 4.1 የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ*

| የትምህርት ቤቱ ዓይነት | የመምህራን ብዛት | የትምህርት ደረጃ | | የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት | | የአገልግሎት ልምድ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዲፕሎማ | ዲግሪ | አማርኛ | ሌላ | ከ5_7 አመት | ከ8_10አመት |
| የመንግስት | 2 | 1 | 1 | 2 | 0 | 1 | 1 |
| የግል | 2 | 0 | 2 | 2 | 0 | 1 | 1 |
| ድምር | 4 | 1 | 3 | 4 | 0 | 2 | 2 |

ሠንጠረዠ 4.1 በምልከታው የተካተቱት መምህራን ከመምህራን ዳራዊ ሁኔታ አንጻር ስብጥራቸውን ያሳያል፡፡ የአገልግሎት ልምድን በተመለከተ በምልከታ ከተካተቱ መምህራን ሁለቱ ከ5-7 አመት የሚሆን የስራ ልምድ አላቸው፡፡ ሁለቱ ደግሞ ከ 7-10 አመት የሚሆን የስራ ልምድ አላቸው፡፡ የትምህርት ደረጃን በተመለከተ ደግሞ ሶስቱ መምህራን ዲግሪ ሲኖራቸው አንዱ ደግሞ ዲፕሎማ አለው፡፡ ይህም ለጥናቱ የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ለመስጠት የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ አዎንታዊ ዕድል ፈጥሯል።

## 4.2 የተጠኝ ተማሪዎች ጳራዊ መግለጫ

*ሠንጠረዠ 4.2 የተጠኝ ተማሪዎች ጳራዊ መግለጫ*

| የትምህርት ቤቱ ዓይነት | ጾታ | |
|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት |
| የመንግስት | 14 | 22 |
| የግል | 16 | 20 |
| ድምር | 30 | 42 |

ሠንጠረዥ 4.2 በጳሰሳ ጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎችን ከተማሪዎች ጳራዊ ሁኔታ አንጻር ስብጥራቸውን ያሳያል፡፡ ከግል ትምህርት ቤት በመጠይቅ ተደራሽ ከሆኑት ተማሪዎች ወንዶቹ አስራስድስት ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ ሀያ ነበሩ፡፡ በአንጻሩ በመንግስት ትምህርት ቤት በመጠይቁ ከተካተቱት ውስጥ አስራ አራቱ ወንዶች ሲሆኑ ሀያ ሁለቱ ሴቶች ናቸው፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤት የተካተቱት የወንዶችና የሴቶች ብዛት ከአጠቃላይ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙት ወንድና ሴት ተማሪዎች አንጻር ስብጥሩ ተመጣጣኝ ነበር፡፡ የተወሰደው ናሙና የትምህርት ቤቶችን ወንድና ሴት ተማሪዎችን የሚወክል መሆኑን ያሳየናል፡፡

## 4.3. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር

ይህ ጥናት በሁለቱ የተመረጡ የግልና የምንግስት ትምህርት ቤቶች ከአንድ በላይ በሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ማለትም ምልከታን፣ ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅና ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅን በመጠቀም የቅድመ ንባብ አተገባበርን ተፈትሿል፡፡ በተጨማሪም የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስትን ተጠቅማለች።

### 4.3.1. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር በቅድመ ንባብ ደረጃ (ከምልከታ አንፃር)

ከምልከታ አንፃር የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተገልጿል (ሠንጠረዥ4.3)

*ሠንጠረዥ 4.3: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች (በቅድመ ንባብ ደረጃ)*

| ተ.ቁ | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርትቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 1.1 | የምንባቡን ርዕስ በግልፅ ማብራራትና መተንተን | 9.01 | 0.657 | 4.78 | 0.854 |
| 1.2 | ለተማሪዎች የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መስጠት ሃሳብ የማፍለቅ ብልሃትን መጠቀም' በቡድንና በተናጠል እንዲሰሩ መቀስቀስ | 3.98 | 0.839 | 2.31 | 0.899 |
| 1.3 | በምንባቡ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ትርጉም እንዲተነብዩ ማድረግ | 9.45 | 0.598 | 4.91 | 0.865 |
| 1.4 | ስለ ምንባቡ ተገቢ የሆነ ፍንጭ መስጠት | 9.68 | 0.497 | 6.21 | 0.966 |
| 1.5 | ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ተጠቅሞ ማስተማር | 9.65 | 0.559 | 6.01 | 0.948 |
| 1.6 | ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብና ዋና ሃሳብን ነጥለው እንዲያወጡ ማድረግ | 4.98 | 0.788 | 3.31 | 0.953 |
| 1.7 | ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትንና ምክንያታዊ ብልሃትን መጠቀም | 4.52 | 0.812 | 2.58 | 0.978 |
| | ጠቅላላ አማካይ | 7.3 | | 4.3 | |

ለጥናቱ በተመረጠው ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመባል በሚታወቀው የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ሲተገብሩ በምልከታ ተስተውሏል። መምህራኑ ስለ ምንባቡ ተገቢ የሆነ ፍንጭ ይሰጣሉ። በተጨማሪም ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ተጠቅመው ያስተምራሉ። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 4.3 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካኝ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 6.21 (0.966) ና 6.01 (0.948) በቅደም ተከተል ተመላክቷል (ሠንጠረዥ4.3) ።

ለጥናቱ በተመረጠው ሆሊሴቨር በመባል በሚታወቀው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም እነዚህን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ሲተገብሩ በምልከታ ተስተውሏል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 7.3 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 9.68 (0.497) ና 9.65 (0.559) በቅደም ተከተል ተመላክቷል (ሠንጠረዥ4.3) ።

በተቃራኒው ለተማሪዎች የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መስጠት ሃሳብ የማፍለቅ ብልሃትን መጠቀምና በቡድንና በተናጠል ተማሪዎች እንዲሰሩ መቀስቀስ የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች እምብዛም ሲተገበር አልታየም። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 4.3 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 2.31 (0.899) ተመላክቷል (ሠንጠረዥ4.3) ። በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 7.3 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 3.98 (0.839) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.3)

በተጨማሪም "ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትንና ምክንያታዊ ብልሃትን መጠቀም" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ሲተገብሩ አልተስተዋለም። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 4.3 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 2.58 (0.978) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.3) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 7.3 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 4.52 (0.812) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.3)

***ሰንጠረዥ 4.4: በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር (በአማካይና መ ደበኛ ልይይት)***

| ተ.ቁ | የአንብቦ መረዳት ብ ልሃቶች | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ል ይይት | አማካይ | መደበኛ ልይ ይት |
| 1 | በቅድመ ንባብ ደረጃ | 7.3 | 0.734 | 4.3 | 0.867 |

በሠንጠረዡ ውጤት እንደምናየው መደበኛ ልይይቱ ከአንድ በታች ነው፣ ይህ ደግሞ ኖርማል ዲስትሪቡሽን ከማሳየቱ ባሻገር በቅድመ ንባብ ደረጃ ላሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የተሰጡት ምልከታዎች በአማካይ ውጤቱ ዙሪያ መሆናቸውንም ያሳያል። ይህም ወደ ትንታኔ እንዲገባ ይጋብዛል። ከስድስት ምልከታ መረጃ በመነሳት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በመተግበር ረገድ ካስመዘገቡት አማካይ 4.3 መደበኛ ልይይት 0.867 የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያስመዘገቡት አማካይ 7.3 መደበኛ ልይይት 0.734 ብልጫ አሳይቷል።

በመቀጠል ከዚህ ምልከታ ውጤት በመነሳት በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ በባለ ሁለት ጫፍ የተሰላውን የጉልህነት ውጤትና የዝምድና ጥንካሬ ተፈትሿል። የዚህም ውጤት እንደሚከተለው ነው።

*ሠንጠረዥ 4.5: ቲ-ቴስት (በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ)*

| የመንግስት ትምህርት ቤት | | የግል ትምህርትቤት | | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት | የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 4.3 | 0.867 | 7.3 | 0.734 | 2.96 | 2 | 0.035 | 2.9 |

ከላይ ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው የባለ ሁለት ጫፍ ጉልህ ውጤት ከ 0.05 ያነሰ በመሆኑ በቅድመ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ከመተግበር አኳያ በሁለቱ ትምህ ት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

### 4.3.2. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በጊዜ ንባብ ደረጃ (ከምልከታ አ ንፃር)

ከምልከታ አንፃር የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተገልጿል (ሠንጠረዥ4.6)

*ሠንጠረዥ 4.6: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በጊዜ ንባብ ደረጃ*

| ተ.ቁ | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይ ይት |
| 2.1 | ምስል የመከሰት ብልሃት ተጠቅ መው እንዲያነቡ ማድረግ | 7.68 | 0.411 | 4.59 | 0.799 |
| 2.2 | አንድምታና ትንበያ ብልሃትን እንዲጠቀሙ ማድረግ | 6.99 | 0.565 | 3.53 | 0.956 |
| 2.3 | ደጋግሞ የማንበብ ብልሃትን መ ጠቀምና የምንባቡን መንስኤና ውጤት የነገሮችንም አንድነትና ልዩነት እንደለዩ ማስተማር | 14.88 | 0.387 | 9.15 | 0.698 |
| 2.4 | የማጠቃለያና የመደምደሚያ ብ ልሃቶትን ተጠቅመው እንዲያነቡ ማስተማር | 14.99 | 0.317 | 9.37 | 0.599 |
| 2.5 | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተ ማሪዎች በራሳቸው እንዲመርጡ ማድረግ | 6.89 | 0.771 | 4.29 | 0.768 |
| 2.6 | የምንባቡን ሃሳብ በፍጥነት የማግ ኘት ብልሃትን ማስተማር | 6.78 | 0.602 | 3.49 | 0.999 |
| 2.7 | በመጽሃፍ የተካተቱ ይዘቶችን ለ መተግበር ተስማሚ ብልሃትን አ ጢኖ መጠቀም | 7.59 | 0.448 | 3.58 | 0.894 |
| ጠቅላላ አማካይ | | 9.4 | | 5.4 | |

ለጥናቱ በተመረጠው ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ሲተገብሩ ምልከታ ተደርጓል። መምህራኑ ተማሪዎች የማጠቃለያና የመደምደሚያ ብልሃቶችን ተጠቅመው እንዲያነቡ ያስተምራሉ። በተጨማሪም መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ደጋግሞ የማንበብ ብልሃትን እንዲጠቀሙና የምንባቡን መንስኤና ውጤት የነገሮችን አንድነትና ልዩነት እንዲለዩ ያስተምሯቸዋል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 5.4 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 9.37 (0.599) ና 9.15 (0.698) በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.6)

ለጥናቱ በተመረጠው ሆሊሴቨር የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም እነዚህን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ሲተገብሩ ምልከታ ተከናውኗል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 9.4 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 14.99 (0.317) ና 14.88 (0.387) በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.6)

በተቃራኒው የምንባቡን ሃሳብ በፍጥነት የማግኘት ብልሃትን ማስተማር" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች እምብዛም ሲተገበር አልታየም። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 5.4 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 4.29 (0.768) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.6) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 9.4 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 6.89 (0.771) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.6)

በተጨማሪም አንድምታና ትንበያ ብልሃትን እንዲጠቀሙ ማድረግ" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ሲተገብሩ አልተስተዋለም። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 5.4 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 4.59 (0.799) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.6) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 9.4 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 6.99 (0.565) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.6)

*ሠንጠረዥ4.7: በጊዜ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር (በአማካይና መደበኛ ልይይት)*

| ተ.ቁ | የንባብ ደረጃ አተገባበር | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 1 | በጊዜ ንባብ ደረጃ | 9.4 | 0.734 | 5.4 | 0.976 |

ከስድስት ምልከታ መረጃ በመነሳት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጊዜ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በመተግበር ረገድ ካስመዘገቡት አማካይ 5.4 መደበኛ ልይይት 0.976 የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያስመዘገቡት አማካይ 9.4 መደበኛ ልይይት 0.734 ብልጫ አሳይቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.7)

በመቀጠል ከዚህ ምልከታ ውጤት በመነሳት በጊዜ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ቲ-ቴስት ተከናውኗል፡፡ ውጤቱም ከታች በተገለፀው ሰንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል።

*ሠንጠረዥ 4.8: ቲ-ቴስት (በንባብ ጊዜ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ)*

| የመንግስት ትምህርት ቤት | | የግል ትምህርትቤት | | የ t-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የባለ ሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት | የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 5.4 | 0.976 | 9.4 | 0.734 | 1.987 | 2 | 0.075 | የለም |

ከላይ ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው የባለ ሁለት ጫፍ ጉልህ ውጤት ከ 0.05 በላይ በመሆኑ ከንባብ ጊዜ አተገባበር አኳያ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት የለም።

### 4.3.3. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በድህረ ንባብ ደረጃ (ከምልከታ አንፃር)

ከምልከታ አንፃር የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተገልጿል (ሠንጠረዥ4.9)

*ሠንጠረዥ4.9: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በድህረ ንባብ ደረጃ*

| ተ.ቁ | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 3.1 | ያነበቡትን ምንባብ የማብራራት የመተርጎ ምና የመተንተን ብልሃትን መጠቀም | 10.55 | 0.999 | 5.679 | 1.045 |
| 3.2 | በድህረ ንባብ ጊዜ ስላነበቡት ነገር እንዲ ተነትኑና እንዲያብራሩ ማድረግ | 10.64 | 0.987 | 6.01 | 0.915 |
| 3.3 | በቅድመ ንባብ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት መግለፅ | 14.69 | 0.789 | 8.99 | 0.889 |
| 3.4 | እርስ በርሳቸዉ እንዲወያዩ እንደገና እንዲ ናገሩ አድርጎ ማስተማር | 10.13 | 1.345 | 5.345 | 1.567 |
| ጠቅላላ አማካይ | | **11.5** | | **6.5** | |

ለጥናቱ በተመረጠው ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚከተለውን የአንብቦ መረዳት ብልሃት ሲተገብሩ ምልከታ ተደርጓል። መምህራኑ ተማሪዎች በቅድመ ንባብ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ይገልፃሉ። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 6.5 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 8.99 (0.889) ተመላክቷል (ሠንጠረዥ 4.9) ።

ለጥናቱ በተመረጠው ሆሊ ሴቨር በመባል በሚታወቀው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም ይህን የአንብቦ መረዳት ብልሃት ሲተገብሩ በምልከታ ተስተውሏል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 11.5 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 14.69 (0.789) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.9)

በተቃራኒው "እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ እንደገና እንዲናገሩ አድርጎ ማስተማር" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች እምብዛም ሲተገበር አልታየም። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 6.5 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካኝ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 5.345 (1.567) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.9) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 11.5 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካኝ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 10.13 (1.345) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.9)

***ሠንጠረዥ 4.10 በድህረ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር (በአማካይና መደበኛ ልይይት)***

| ተ.ቁ | የንባብ ደረጃ አተገባበር | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 1 | በድህረ ንባብ ደረጃ | 11.5 | 1.234 | 6.5 | 1.109 |

በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በድህረ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በመተግበር ረገድ ካስመዘገቡት አማካይ 6.5 መደበኛ ልይይት 1.109 የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያስመዘገቡት አማካይ 11.5 መደበኛ ልይይት 1.234 ብልጫ አሳይቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.10)

በመቀጠል ከዚህ ምልከታ ውጤት በመነሳት በድህረ ንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ በባለ ሁለት ጫፍ የተሰላውን የጉልህነት ውጤትና የዝምድና ጥንካሬ ተፈትሿል፡፡ ውጤቱም ከታች በተገለፀው ሰንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል።

*ሠንጠረዥ 4.11፡ ቲ-ቴስት (በድህረንባብ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በ ተመለከተ)*

| **የመንግስት ትምህርት ቤት** | | **የግል ትምህር ቤት** | | **የ t-ዋጋ** | **የነፃነት ደረጃ** | **የባለ ሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት** | **የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **አማካይ** | **መደበኛ ልይይት** | **አማካይ** | **መደበኛ ልይይት** | | | | |
| 5.4 | 0.976 | 9.4 | 0.734 | 3.109 | 2 | 0.045 | 2.432 |

ከላይ ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው የባለ ሁለት ጫፍ ጉልህ ውጤት ከ 0.05 ያነሰ በመሆኑ ከድህረ ንባብ አተገባበር አኳያ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

## 4.4. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ጠቅላላ ውጤት (ከምልከታ አንፃር)

ከምልከታ አንፃር ጥቅል ውጤቱ በባለ ሁለት ጫፍ የተሰላውን የጉልህነት ውጤት ና የዝምድና ጥንካሬ ጨምሮ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡ (ሠንጠረዥ4.12)

*ሠንጠረዥ 4.12፡ ቲ-ቴስት (በሁሉም ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በ ተመለከተ (ከምልከታ አንፃር)*

| **የመንግስት ትምህርት ቤት** | | **የግል ትምህርት ቤት** | | **የ t- ዋጋ** | **የነፃነት ደረጃ** | **የባለ ሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት** | **የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **አማካይ** | **መደበኛ ልይይት** | **አማካይ** | **መደበኛ ልይይት** | | | | |
| 16.2 | 0.999 | 28.2 | 0.777 | 2.987 | 2 | 0.009 | 1.39 |

ከላይ ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው የባለ ሁለት ጫፍ ጉልህ ውጤት ከ 0.05 ያነሰ በመሆኑ በሁሉም የንባብ ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር በሁለቱ ትምህርትቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

### 4.4.1. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)

#### 4.4.1.1 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በቅድመ ንባብ ደረጃ (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)

ለተማሪዎች ከቀረበረው የጽሑፍ መጠይቅ አንፃር በቅድመ ንባብ ደረጃ የተገኘው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ውጤት እንደሚከተለዉ ተገልጿል፡፡ (ሠንጠረዥ4.13)

*ሠንጠረዥ 4.13: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በቅድመ ንባብ ደረጃ (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)*

| ተ/ቁ | የአንብቦ መረዳት ብልቶች አተገባበር | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 1.1 | የምንባቡን ርዕስ በግልፅ ማብራራትና መተንተን | 17 | 0.453 | 16 | 0.533 |
| 1.2 | ለተማሪዎች የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መስጠት ሀሳብ የማፍለቅ ብልሀትን መጠቀም' በቡድንና በተናጠል እንዲሰሩ መቀስቀስ | 8 | 0.501 | 7 | 0.599 |
| 1.3 | በምንባቡ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ትርጉም እንዲተነብዩ ማድረግ | 27 | 0.413 | 26 | 0.529 |
| 1.4 | ስለ ምንባቡ ተገቢ የሆነ ፍንጭ መስጠት | 32 | 0.399 | 31 | 0.499 |
| 1.5 | ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ተጠቅሞ ማስተማር | 30 | 0.409 | 29 | 0.511 |
| 1.6 | ድምፅን ከፍ አድርጎማንበብና ዋና ሃሳብን ነጥለው እንዲያወጡ ማድረግ | 10 | 0.487 | 9 | 0.544 |
| 1.7 | ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትንና ምክንያታዊ ብልሃትን መጠቀም | 9 | 0.499 | 8 | 0.555 |
| ጠቅላላ አማካይ | | 19 | | 18 | |

ለጥናቱ በተመረጠው ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመባል በሚታወቀው የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራኖቻቸው የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አብዛኛውን ጊዜ እንደሚተገብሩ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። መምህራኑ ስለ ምንባቡ ተገቢ የሆነ ፍንጭ ይሰጣሉ። በተጨማሪም ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ተጠቅመው ያስተምራሉ። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 18 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 31 (0.499) ና 29 (0.511) በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.13)

ለጥናቱ በተመረጠው ሆሊሴቨር በመባል በሚታወቀው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኖቻቸው እነዚህን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እንደሚተገብሩ መስክረውላቸዋል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 19 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 32 (0.399) ና 30 (0.409) በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.13)

በተቃራው ለተማሪዎች የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መስጠት ሃሳብ የማፍለቅ ብልሃትን መጠቀም'ና በቡድንና በተናጠል ተማሪዎች እንዲሰሩ መቀስቀስ የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው አልፎ አልፎ እንጂ እምብዛም እንደማይተገብሯቸው መስክረዋል።

ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 18 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካኝ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 7 (0.599) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.13) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 19 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 8 (0.501) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.13)

በተጨማሪም "ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትንና ምክንያታዊ ብልሃትን መጠቀም" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው እምብዛም እንደማይተገብሯቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 18 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 8 (0.555) ተመላክቷል (ሠንጠረዥ4.13)። በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 19 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 9 (0.499) ተመላክቷል (ሠንጠረዥ4.13)።

#### 4.4.1.2. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በጊዜ ንባብ ደረጃ (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)

ለተማሪዎች ከቀረበረው የጽሑፍ መጠይቅ አንፃር በጊዜ ንባብ ደረጃ የተገኘው የአን ብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ውጤት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡ (ሠንጠረዥ 4.14)

*ሠንጠረዥ 4.14 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በጊዜ ንባብ ደረጃ*

| ተራ ቁጥር | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ዝርዝር ተግባራት | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 2.1 | ምስል የመከሰት ብልሃት ተጠቅመው እንዲያነቡ ማድረግ | 31 | 0.337 | 28 | 0.322 |
| 2.2 | አንድምታና ትንበያ ብልሃትን እንዲጠቀሙ ማድረግ | 16 | 0.366 | 15 | 0.399 |
| 2.3 | ደጋግሞ የማንበብ ብልሃትን መጠቀምና የምንባቡን መንስኤና ውጤት የነገሮችን አንድነትና ልዩነት እንደለዩ ማስተማር | 53 | 0.199 | 51 | 0.299 |
| 2.4 | የማጠቃለያና የመደምደሚያ ብልሃቶችን ተጠቅመው እንዲያነቡ ማስተማር | 50 | 0.211 | 48 | 0.301 |
| 2.5 | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተማሪዎች በራሳቸው እንዲመርጡ ማድረግ | 19 | 0.364 | 16 | 0.356 |
| 2.6 | የምንባቡን ሃሳብ በፍጥነት የማግኘት ብልሃትን ማስተማር | 14 | 0.388 | 13 | 0.432 |
| 2.7 | በመጽሃፍ የተካተቱ ይዘቶችን ለመተግበር ተስማሚ ብልሃትን አጢኖ መጠቀም | 27 | 0.349 | 25 | 0.333 |
| | ጠቅላላ አማካይ | 30 | | 28 | |

ለጥናቱ በተመረጠው ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመባል በሚታወቀው የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራኖቻቸው የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አብዛኛውን ጊዜ እንደሚተገብሩ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። መምህራኖቻችን እኛ የማጠቃለያና የመደምደሚያ ብልሃቶችን ተጠቅመን እንድናነብ ያስተምሩናል። በተጨማሪም መምህራኑ እኛ ደጋግሞ የማንበብ ብልሃትን እንድንጠቀምና የምንባቡን መንስኤና ውጤት የነገሮችንም አንድነትና ልዩነት እንድንለይ ያስተምሩናል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 28 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 51 (0.299) ና 48 (0.301) በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.14)

ለጥናቱ በተመረጠው ሆሊሲቨር በመባል በሚታወቀው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኖቻቸው እነዚህን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እንደሚተገብሩ መስክረውላቸዋል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 9.4 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 53 (0.199) ና 50 (0.211) በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.14)

በተቃራኒው የምንባቡን ሃሳብ በፍጥነት የማግኘት ብልሃትን ማስተማር የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው አልፎ አልፎ እንጂ እምብዛም እንደማይተገብሯቸዉ መስክረዋል። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 28 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 13 (0.432) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.14) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 30 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካኝ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 14(0.388) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.14)

በተጨማሪም "አንድምታና ትንበያ ብልሃትን እንዲጠቀሙ ማድረግ" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው እምብዛም እንደማይተገብሯቸ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 28 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 15 (0.399)

ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.14) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 9.4 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 16 (0.366) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.14)

#### 4.4.1.3. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር - በድህረ ንባብ ደረጃ (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)

ለተማሪዎች ከቀረበረው የጽሑፍ መጠይቅ አንፃር በድህረ ንባብ ደረጃ የተገኘው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ውጤት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡ (ሠንጠረዥ4.15)

*ሠንጠረዥ 4.15: የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች - በድህረ ንባብ ደረጃ*

| ተራ ቁጥር | የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ዝርዝር ተግባራት | የግል ትምህርት ቤት | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
| 3.1 | ያነበቡትን ምንባብ የማብራራት የመተርጎምና የመተንተን ብልሃትን መጠቀም | 39 | 0.222 | 34 | 0.297 |
| 3.2 | በድህረ ንባብ ጊዜ ስላነበቡት ነገር እንዲተነትኑና እንዲያብራሩ ማድረግ | 55 | 0.198 | 48 | 0.244 |
| 3.3 | በቅድመ ንባብ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት መግለፅ | 59 | 0.111 | 50 | 0.199 |
| 3.4 | እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ እንደገና እንዲናገሩ አድርጎ ማስተማር | 35 | 0.299 | 32 | 0.333 |
| ጠቅላላ አማካይ | | 47 | | 41 | |

ለጥናቱ በተመረጠው ብርሀነ ጎሊና የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመባል በሚታወቀው የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራኖቻቸው የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አብዛኛውን ጊዜ እንደሚተገብሩ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። መምህራኖቻችን

እኛ ተማሪዎች በቅድመ ንባብ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ የሚያጋጥሙንን አዳዲስ ቃላት ይገልፁልናል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 41 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 50 (0.199) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.15)

ለጥናቱ በተመረጠው ሆሊሴቨር በመባል በሚታወቀው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኖቻቸው እነዚህን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እንደሚተገብሩ መስክረውላቸዋል። ይህም ከጠቅላላ አማካይ 47 ብልጫ በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 59 (0.111 ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.15)

በተቃው "እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ እንደገና እንዲናገሩ አድርጎ ማስተማር" የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው እምብዛም እንደማይተገብሯቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ይህም በመንግስት ትምህርት ቤት ከጠቅላላ አማካይ 41 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 32 (0.333) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.15) በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ከጠቅላላ አማካይ 47 አንፃር አነስተኛ ውጤት በሚያሳይ መልኩ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት 35 (0.299) ተመላክቷል፡፡ (ሠንጠረዥ4.15)

4.5 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ጠቅላላ ውጤት (ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር) ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ አንፃር ጥቅል ውጤቱ በባለ ሁለት ጫፍ የተሰላውን የጉልህነት ውጤትና የዝምድና ጥንካሬ ጨምሮ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

*ሠንጠረዥ 4.16፡ ቲ-ቴስት (በሁሉም ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በ ተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቅ አንፃር)*

| የመንግስት ትምህ ርት ቤት | | የግል ትምህርትቤት | | የ ቲ- ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የባለሁለ ት ጫፍ የጉልህነ ት ውጤ ት | የዝም ድና ጥንካሬ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማካ ይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 29 | 0.789 | 32 | 0.668 | 2.76 | 2 | 0.033 | 2.76 |

ከላይ ሠንጠረገፑ እንደሚያሳየው የባለ ሁለት ጫፍ ጉልህ ውጤት ከ 0.05 ያነሰ በመሆኑ በሁሉም የንባብ ደረጃ አተገባበሮች ማለትም በቅድመ ንባብ አተገባበር፣ በንባብ ጊዜ አተገባበር፣ በድህረ ንባብ አተገባበር በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

## 4.5 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ማብራሪያ

በሌላ በኩል ለሁለቱ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከጥናቱ አኳያ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ በዓይነታዊ የትንተና ዘዴ በመተንተን እንደሚከተለው ቀርቧል። በዚህም መሰረት  ለጥናቱ ከተመረጡት ሁለት የግልና የመንግስት መምህራን በቃለ መጠይቅ ሁሉም ሲሳተፉ በመጀመሪያ በማስተማር ሙያ ላይ እያሉ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር በተመለከተ የስራ ላይ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም መመህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር በተመለከተ ስልጠና እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡ መ1፣ግ2 በኮሌጅና በልምድ ባገኘነው ነው የምንሰራው ሲሉ <u>መ2</u> ፣ <u>ግ1</u> ደግሞ ስልጠና ቢሰጠን ጥሩ ነበር ወደ ስራ ለመግባት ያበረታታል ለክሂሉ ትኩረት እንድንሰጥ ያበረታታናል በማለት መልሰዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ደግሞ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ክሂል ለማሻሻል ምን ምን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተጠቅመው ያስተምራሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ደግሞ <u>ግ1</u> የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል

ለማሻሻል የምጠቀመው የማስተማሪያ ብልሃት ወይም ስልት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ሌሎች ተማሪዎች ማስታወሻ በመያዝ ያዳመጡትን በቃል እንዲናገሩ በማድረግ ጥያቄና መልስ እንዲያደርጉ በማድረግ፣ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ፤ ቃላትን በአውዳቸው እንዲናገሩ በማድረግ፣ የፕሮጀክት ስራ ሰርተው በመምጣት በቃል እንዲያቀርቡ በማድረግ አስተምራለሁ፡፡ መ1 የምጠቀማቸው የማስተማሪያ ብልሃቶች የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ፣ ጥያቄና መልስ በመማሪያ መፅሃፋቸው ላይ ያለውን ምንባብ በተናጠል በማስነበብ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በማድረግ አስተምራለሁ፡፡ ሲሉ መ2 ለተማሪዎች የሚነበቡ ፅሁፎችን በመስጠት የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ፣የንባቡን ሀሳብ በአጭሩ እንዲፅፉ በማድረግና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በማሰራት አስተምራለሁ፡፡

ግ2 ደግሞ በመማሪያ መፅሀፋቸው የቀረበውን ምንባብ መጀመሪያ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል በመጠየቅና ከዚህ በኋላ ምንባቡን ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ ከቅድመ ጥያቄው ጋር መልሳቸውን በማሰራት አስተምራለሁ በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል ከመምህራኖቹ ምላሽ መረዳት እንደቻልኩት የግል ትምህርት ቤት መምህራን የሚጠቀሙት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ማስታወሻ መያዝ፣ የፅሁፉን ሃሳብ መናገር፣ጥያቄና መልስ ፣ ድህረ ምንባብ ሲጠቀሙ ፤ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ደግሞ የሚጠቀሟቸው ቅደመ ምንባብ ጥያቄና መልስ ፣ምንባብን በተናጠል ማስነበብ፣ የድህረ ምንባብ ጥያቄ ፣የምንባብ ሃሳብን በአጭሩ እንዲፅፉ ማድረግ ብልሃቶችን እንደተጠቀሙ ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚህ የቃለ መጠይቅ መልስ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም መምህራን በተገቢው መንገድ ተገቢ የሆነውን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች መጠቀም እንዳልቻሉ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በክፍል ምልከታና በተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሶስተኛው ተራ ቁጥር የቀረበው ጥያቄ ማለትም የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ተማሪዎች የሚማሩትን የአንብቦ መረዳት ትምህርት የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ይጠቅማል ብለው ያምናሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም መምህራን በትክክል ከተተገበረ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማዳበር ይጠቅማሉ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ የመምህራኑን መልስ ከምሁራን አስተያየት ጋር ተጣጥሞ ቀርቧል፡፡ Oxford (1990) እንደሚሉት የመማር ብልሃቶች በተማሪዎች ሆን ተብለው የሚመረጡ፣መማርን ለማፋጠን ወይም በቋንቋው መረጃን ለማሳካት ፣ለማስታወስ እና በተግባር ለመጠቀም የሚያገለግሉ ሂደቶች ናቸው፡፡

የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች የሚማሩበትን ትምህርት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ናቸው ቀላል፣አዝናኝ እና ነገሮችን በራስ ተነሳስቶ በማስተካከል ወደ አዲስ እውቀት ለመሸጋገር የሚያስችሉ ተግባራትም ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ የመምህራኑን መልስ ከምሁራን አስተያየት ጋር ተጣጥሞ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የመማር ብልሃቶችን ሲጠቀሙ ቀላልም ሆነ ከባድ ተግባራት ተማሪዎችን ሲያሰሩ የተለየ ጉልበት እና ጊዜ ሳያወጡ እንደመማር ብልሃት ምርጫቸው የሚያከናውኑባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡

በመጨረሻም እርሶ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳትጠቀሙ የሚያደርጉ ችግሮች አሉ? ካሉ ይዘርዝሩ ሁሉም መምህራን አዎ አሉ በማለት ምላሻቸውን ሲሰጡ ግ1 በመማሪያ መፅሀፋቸው የቀረቡ ምንባቦችን ሳስነብብ ብልሃቶቹን ለመጠቀም የግንዛቤ እጥረት እና የጊዜ እጥረት የተማሪዎች መፅሀፍ አለመኖሩን ጠቅሰዋል፡፡ <u>ግ2</u> መፅሃፍ ውስጥ ያለው የፅሁፍ መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ ጋር አለመመጣጠን ፣የተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ አለመኖር፣ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን አውቄ የትኛውን በምን ጊዜና ሰዓት መጠቀም እንዳለብኝ ተረድቼ /ተዘጋጅቼ/ አለመግባት በማለት መልሰዋል፡፡ መ1 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ከደረጃዎቹና ስልቶቹ ጋር ያላቸውን ልዩነት አለመረዳት፣ የተማሪዎች ተነሳሽነት ማነስ የኔንም የማስተማር ፍላጐት ቀንሶታል፡፡ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ <u>መ2</u> የንባብ ክሂልን ሳስተምር የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተጠቅሜ አላውቅም፡፡ አላውቃቸውም ንባብን ሳስተምር የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እሰራለሁ፤ ተማሪዎች ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ ከዚያ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እሰራለሁ ከዚያ እጨርሳለሁ፡፡ እኔም የዝግጅት ችግር አለብኝ መፅሀፉን ለመጨረስ ብቻ ነው እንጂ ምንባቡን ተረዱት አልተረዱት ትኩረት አላደርግም፡፡ በተጨማሪ ግን የምለው ነገር ቢኖር በብልሃቶቹ ላይ የስራ ላይ ስልጠና ቢኖርና ቢሰጠን የአንብቦ

መረዳት ብልሃቶችን አውቄ በአግባቡ በመተግበር ውጤታማ እሆናለሁ ብዬ አምናለሁ፡፡

በአጠቃላይ የሁሉም ምህራን መልስ እንደሚያስረዳው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ያጋጠሟቸው ችግሮች ፡- የግንዛቤ ችግር ፣ የመፅሀፍ ፣የጊዜ እጥረት ስላለ መፅሀፉን ለመጨረስ እንጂ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ላይ ትኩረት እንደማያደርጉ ፣ የተማሪዎችና የመምህራን ተነሳሽነት አለመኖር ፣ ብልሃቶቹን በሚገባ አውቀው መቼና እንዴት እንደሚተገብሩ አለመረዳት ፣ ብልሃቶቹን ከደረጃዎቹ ጋር ማመሳሰል፣ በመንግስት ትምህርት ቤት የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ የዝግጅት ማነስ እንዳለባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የምንመርጠው የፅሁፍ መጠን በክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጠመ መሆን አለበት፡፡

## 4.6. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በሚመለከት የዚህ ጥናት ውጤት በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። ቀደም ካሉ የጥናት ውጤቶች ጋር ሲመሳከር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ለምሳሌ ጌታቸው (2013) የተባሉት ምሁር ከዚህ ጋር ተማሳይነት ያለው ውጤት ይፋ አድርገዋል።

በዚህ ጥናት የተገኘው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር አማካይ ቀደም ሲል ከተገኙ ውጤቶች አንፃር ሲነፃፀር እጅግ ያነሰ ነው። ይህ ደግሞ በሁለቱም ማለትም ለዚህ ጥናት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ታይቷል። ከዚህ ቀደም ከተጠኑት ጥናቶች ውጤት አንፃር ስንመዝነው በቅድመ ንባብ ደረጃ በርከት ያሉት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ሲተገበሩ አልተስተዋለም ከእነዚህም ውስጥ ለምሳሌ ለተማሪዎች የቅድመንባብ ጥያቄዎች መስጠት'ሃሳብ የማፍለቅ ብልሃትን መጠቀም" በቡድንና በተናጠል እንዲሰሩ መቀስቀስ' ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብና ዋና ሃሳብን ነጥለው እንዲያወጡ ማድረግና ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትንና ምክንያታዊ ብልሃትን መጠቀም የመሳሰሉት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እምብዛም በመምህራኑ የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ አልታዩም።

ሌላው በጊዜ ንባብ ደረጃ የሚከተሉት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ማለትም ተማሪዎች አንድምታና ትንበያ ብልሃትን እንዲጠቀሙ ማድረግ' የምንባቡን ሃሳብ በፍጥነት የማግኘት ብልሃትን ማስተማርና በመጽሃፍ የተካተቱ ይዘቶችን ለመተግበር ተስማሚ ብልሃት አጢኖ መጠቀም በመምህራኑ የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ እምብዛም አልተስተዋለም።

በተጨማሪም በድህረ ንባብ ደረጃ የሚከተሉት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ማለትም ያነበቡትን ምንባብ የማብራራት የመተርጎምና የመተንተን ብልሃትን መጠቀምና ተማሪዎችእርስ በርሳቸው እንዲወያዩ እንደገና እንዲናገሩ አድርጎ ማስተማርን በመምህራኑ የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ እምብዛም አልተስተዋለም።

ከዚህ ቀደም ከታዩት ውጤቶች አንፃር በዛ ያሉትን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መተግበር ያልቻሉበት ምክንያት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማለትም መጽሀፍት በበቂ መገኘት አለመቻላቸው ነው።ሌላው ደግሞ በስራ ላይ እያሉ ከአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስልጠናዎችን አለመውሰዳቸውን ነው።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የብርሃነ ህሊና ቅድመ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት እንዲሁም ከግል የሆሊሲቪየር ትምህርት ቤት ውስጥ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንፅፅር መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አብይ ዓላማ ከግብ ለማድረስም አራት ንዑሳን አላማዎች ተነድፈዋል፡፡ ከተነደፉት አላማዎች ጋር ዝምድና ያላቸው ንድፈ ሃሳቦች በምዕራፍ ሁለት ቀርበዋል፡፡በምዕራፍ ሦስትም የአጠናን ሂደት ተገልጿል፤የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም (ምልከታ፣የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ) ሲሆኑ የተዘጋጁበት ስልትና የአተናተን ዘዴው ተብራርቷል፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በምዕራፍ አራት ስር ተተንትነዋል፡፡በትንተናው የተገኙ ውጤቶችም እንደሚከተለው ጠቅለል ብለው ቀርበዋል፡፡

5.1.1 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን ለማሻሻል በተገቢውና በሚፈለገው መጠን ያነበቡትን ምንባብ ሃሳብ ለመረዳትና የማንበብ ችሎታቸውንም ጭምር ለማዳበር የሚያስችል እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ መምህራን የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የመጠቀም አቅም በማጎልበት ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ (ይወጣሉ)፡፡ የትኛው ብልሃት የንባብ ጊዜ መጠቀም እንደሚችሉ ማበረታታትና በሚያስተምሩበት ወቅትም ብልሃቶችን እየተጠቀሙ ማስተማር ተማሪዎች ብልሃቶቹን የመጠቀም ብቃታቸውን ከፍ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን በጥናቱ እንደታየው መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት ብልሃቶችን በመተግበር ረገድ የአተገባበር ችግር ይስተዋላል፡፡ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሟቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች፡- ስለምንባብ ፍንጭ መስጠት፣ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ፣ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት፣ማጠቃለያና

መደምደሚያ ደጋግሞ ማንበብ፣መንስኤና ውጤት ሲሆኑ፣በአንፃሩ የግል ትምህርት ቤት መምህራንም እነዚህን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች እንደሚተገብሩ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በተገኘ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ በተቃራኒው ሀሳብን በፍጥነት የማግኘት ብልሃት፣ ምስል መከሰት፣ አንድምታ፣ ትንበያ፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ምንያታዊ ብልሃት፣ ሀሳብ ማፍለቅ፣ እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ፣ እንደገና እንዲናገሩ ወዘተ. አድርጎ ማስተማር በሁለቱም ትምህርት ቤቶች እምብዛም እንደማይተገበሩ ተረጋጧል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ቢሆን የግል ት/ቤት መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ አፈፃፀም እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አረጋጧል፡፡

5.1.2 በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችንና መልመጃዎችን ተስማሚ ከሆኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ጋር አገናዝቦ ከማስተማር አንፃር የግል ትምህርት ቤት መምህራንና የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን በምን መልኩ እየተገበሩት እንደሆነ በጥናቱ ተዳሶ፣ሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪዎች በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችንና መልመጃዎችን ከብልሃቶቹ ጋር አገናዝቦ ማስተማር በአግባቡ ሲተገብሩ አልተስተዋለም፡፡ በመሆኑም በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት በቂ ትኩረት የማይሰጠው እንደሆነና የአተገባበር የጎላ ልዩነትም እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡

5.1.3 በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ይዘቶችን ሲተገብሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ እያበረታ ማስተማራቸው ሲፈተሽ፡- የግል ትምህርት ቤት መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ አፈፃፀም እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አረጋጧል፡፡

5.1.4 የንባብ ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ምክንያቶች ሲፈተሹ፡- የሁለቱም ተተኳሪ ትምህርት ቤት መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ምክንያቶች እንዳሉ ተረጋጧል፡፡ ይህም፡- የግል ትምህርት ቤት መምህራን፡- የግንዛቤ እጥረት የተማሪ መፅሐፍ አለመኖር፣ ብልሃቶቹን አለማወቅ፣ የትኛውን በምን ጊዜና ሰዓት መጠቀም እንዳለባቸው ተረድተው (ተዘጋጅተው) አለመግባት ሲሆን፡- የመንግስት ትምህርት ቤት

መምህራን ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ከደረጃዎቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት አለመረዳት ብልሃቶቹን አለማወቅ፣ የተማሪዎች የተነሳሽነት ማነስ፣ የመምህሩ የማስተማር ፍላጎት ማነስ፣ የተማሪ ክፍል ጥምርታው ያለመመጣጠን ለትግበራው እንቅፋት እንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር በትኩረት ማከናወን (መተግበር) ይገባል፡፡ በምልከታ፣ በፅሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን አተገባበር ጥሩ የሚባል አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ምን እንደሆነ በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት መምህራን ብልሃቶቹ ላይ በቂ እውቀት እንደሌላቸውና ባላቸው እውቀትም ተገቢ የሆነ ዝግጅት አድርገው በመግባት ብልሃቶቹን ለመተግበር ዝግጁነት እንደሚያጥራቸውና የስራ ላይ ስልጠና እንደማያገኙ ገልፀዋል፡፡

## 5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት የተገኙትን ውጤቶች መሠረት በማድረግ ማጠቃለያ ከተሰጠ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

5.2.1 የሁለቱም ተተኳሪ ትምህርት ቤት መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሟቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች፡- ጥያቄና መልስ፤ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፣ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ የመሳሉት ሲሆኑ፡-ከዚህ ውጪ ያሉትን እንደምስል መፍጠር፣ እንደገና መናገር፣ ማጠቃለል መገመት፣ ግራፍ ማደራጀት፣ መተንበይ፣ ሚና ጨዋታ የመሳሉትን ብልሃቶች በተገቢው ቦታና ጊዜ መጠቀም ቢችሉ፡፡

5.2.2 የሁለቱም ተተኳሪ ትምህርት ቤት መምህራን የእለቱን የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት በቅድመ ንባብ፣ በንባብና በድህረ ንባብ ጊዜ ብልሃቶቹን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ማቀድ ቢችሉ፡፡

5.2.3 በመንግስት ትምህርት ቤት በክፍል ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ መሆን ሁሉንም በማሳተፍ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ለመተግበር አስቸጋሪ በመሆኑ ትምህርት ቤቱ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ለመማር ማስተማር ምቹ እንዲሆን አድርገው ቢያደራጁ፡፡

5.5.4 የሁለቱም ተተኳሪ መምህራን ብልሃቶቹን እንዴትና መቼ የቱን መጠቀም እንዳለባው የግንዛቤ እጥረት ስለሚታይና መምህራኑም ይህንን በቃለ መጠይቅ ወቅት ያረጋገጡ በመሆኑ መንገስት ለመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ቢያመቻችላቸው፡፡

5.5.5 በሁለቱም ተተኳሪ ትምህርት ቤት የተማሪዎች መፅሐፍ አለመኖር ለትግበራ አስቸጋሪ በመሆኑ መንግስት የተማሪዎችን መማሪያ መፅሐፍ ቢያሟላ፡፡

5.5.6 መምህራን በኮሌጅ ቆይታቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተጠቅመው ማስተማር እንዲችሉ በቂ እውቀት ይዘው እንዲወጡ ቢያደርጉ፡፡

5.5.7 ለሱፐር ቫይዘሮች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በትምህርት ቤቶች ምልከታ በማድረግና የተሻለ የአተገባበር ደረጃ ካለው ትምህርት ቤት ለሌሎች ትምህርት ቤቶች የልምድ ልውውጥ ቢያመቻቹ፡፡

5.5.8 የሥርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርት አዘጋጆች በሚዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያዳብሩ መልመጃዎችን በማዘጋጀት የራሳቸውን ጥረት ቢያደርጉ፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች


ማረው አለሙ፡፡ (1998)፡፡የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ ባህርዳር ዩንቨርሲቲ፡፡ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

ማረው አለሙና ሰፋ መካ፡፡ (2000) ፡፡ በሙያ መስክ ማስተማርባህርዳር ዩንቨርሲቲ፤የአማርኛ ትምህርት ክፍል (ያልታተመ)::

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (2007) ፡፡ በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡አዲስ አበባ፤ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ.

በጎሰው የሽዋስ፡፡ (2003) ፡፡ "በአዲስ አበባ በተምጡ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ ነባርና ጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክረሂል አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት" በአዲስአበባ ዩንቨርሲቲ አማርኛን በማስተማር ስነዘዴ ትምህርት (TeAm) ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ቀረበ ጥናት (ያልታተመ) ፡፡

ተክላይ ትዕዛዙ፡፡(2000)፡፡በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ፡፡ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ) ፡፡

ታደሰ ዳርገው፣ሙሉጌታ ተካና ማረው አለሙ፡፡(2010)፡፡ የራስ መር መማር ብልሃቶች በማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያላቸው ሚና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሰባተኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡ባህርዳር ዩንቨርሰቲ(ያልታተመ) ፡፡

አለምእሸቱ፡፡(1997)፡፡ የምርምርና መሠረታዊ ዘገባ አፃፃፍ አዲስአበባ፤ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

እንድሪስ አባይ ። (2009)። በቴክስት ውቅር ብልሀቶች በአማርኛ ማንበብን በመማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅዕኖ በ6ኛ ክፍል ተተኳሪነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)

የኔሰው ደሴ ፡፡ (1990)፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋችውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞማ ማስተማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት (ያልታተመ) ፡፡

ይታያል ወርቁ፡፡ (2003)፡፡ "የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች፤በ8ኛ

ክፍል ተተኳሪነት”አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር(ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2009)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ፡፡ (2008)፡፡comet supplmentary Books series አማርኛ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፤አስቴር ነጋ አሳታሚ ደርጅት፡፡

ጉለሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ፡፡ (2022) ፡፡ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር (ያልታተመ)፡፡

ጌታቸው በቀለ ፡፡ (2013) ፡፡ የዘጠነኛ ክፍል የአማሪኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አወዳዳሪ ጥናት በመንግስትናበግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት ጎንደር ዩኒቨርስቲ ፡፡ (ያልታተመ) ፡፡

Ardashavay and Tretter.TR(2013) contributions of individual differences and contextual variables to reading achievement of English language learners:TESOL Quarterly.vol,47.No2 (June 2013) pp. 323 — 351 htt ps// WWW istor.org/stable43267794

Baker.W.& Boonkit K.(2004).Learning strategies in reading and writing EAP contexts regional language center Journal 35(3). 299 — 325.

Barrs.Myra (2000). The Reader in the writer.Reading (United Kingdom Reading Association).July. 54 — 60

Block.C (1993). History of reading instruction.WC colins BLOCK(ed)

-----------(1997). Teaching the language Arts Annotated instructors edition.Boston:Allyn and Bacon.

Brown. D.H (1994). Teaching by principle an interactive approach to language pedagogy Engle wood cliffs.New Jersey.Prentice Hall regents

Davis.F (1995) introducing reading. London. Penguin Groups.

El Essawi.K.(2013) language learning strategies in Arabic as a foregin language text book.Source Al.Arabiyya.Vol.46. pp 37-59 Georgetown university press .https//WWW.jstor.org/stable/43195546

Grabe.W.(1991). Current developments in second language reading research,TSOL Quarterly.25(3) 375 — 406

Grallet.F.(1981). Developing Reading skills.Cambridge:Cambridge university press.

Green Wood .(1987). An Introdution Journal for Teachers of English to speakers of other language .English Language Teaching Journal. 43(4). 308-313

Gunining. T. (2006) "Reading comprehension instructional stearatage." From

http://WWW.nsintel.moe.edu.sq./

Harmar.J. (1990) The practice of English Language Teaching London ;Longman Group .LTD.

-------------- (1991) The practices of English language teaching New York: Longman.VOI 4p25-29

--------------- (2001) The practices of English language Teaching oxford;peaeson educational Limited.

Krashen. Stephn.D and Terrel. T.D. (1983) the natural Approach: Language Acquisition in the classroom California: alemany press.

Kuta.(2008). Reading and writing to learn; strategies Accros the curriculum. USA: Library of congress.

Mei — yun.Y.(1993) Cohesion and the teaching of EFL Reading English Teaching forum Vol.31.No.1.pp12-15

Norton.Donna.E (1997). A case study of Viet bahighschool.Vietnam nationl universitycollege of foreign language.Department of post graduate studies.

Nuttall.G (1982). Teaching and Reading skills in foreign language: London: Heinemann educational Books.LTD

Nuttall.C (1996).Teaching reading skills in a oreign language; oxford.Macmillan publishers limited.

-------------- (2000). Teaching reading skill in a foreign language.oxford Macmillan.perfetti.CA.Landi.N

O.Malley and Chamot (1995) Learning strategies in second Language Acquisition.Cambridge.UK, Camridge university press.vol 86 No 3 pp368-383

O.Malley, J.M and Chamot.Anna.v (1990) Learning strategies In second Languge Acquisition Cambridge; Cambridge university press.

Oxford and Crookall.D (1989).Research on language learning strategies methods, findings, and instructional issues.The modern language jornal, vol.73, No.4 (winter, 1989), pp404-419. https;//WWW.jstor.org/stable /326876

Oxford.R.(1990).Language learning strategies what every teacher should know.New York:New Bury House publishers vol4 No.2

Parra.FJ.(2007) The explicit teaching of socio affective language learning strategies to beginner efl students at the centro Colombo Americano:An action research study.Master`s Thesis Bogta.D.C

Parsons.C.E. and Lyddy.F.(2009) Early reading strategies in Irish and English Evidence from error types.Reading in a foreign Language.21(1).22-36

Pearson.P.D (2009).The roots of Readingcomprehension instruction.in S.E Israel (pp.3-31)

Ratna.A (2014) the use of cognitive Reading strategies to Enhance EFL students Reading comprehension.International.Journal of education (1JE). Vol2.No.1 p.1-11

Ringe.C.(1989). The effective Reading of modern language lendon long man UK LTD.

Rubin.J.(1987).Learner strategies.Theoretical Assumption.Research History and Typology in A Wenden and J.rubin(eds.).learner strategies in language learning.(pp-107- 160).Cambridge;Cambridge university pre

Sandra.(1994)student`s usage reading strategies of education.Adnan Menderse university.AYd in 09 100.Turkey

Shanehan.T.(2006) The national Reading panal Report practical Advice for teachers Learning point.Associates.Chicago.

Shang.H.(2010).Reading strategy use.self —efficacy and EFL reading comprehension. The Asian EFL Journal Quarterly.12 (2) .18-42

Silberstein.s.(1989).Technique and Resources in Teaching Reading: oxford: oxford university press

-------------- (1994) Technique and Resources in Teaching reading NewYork:oxford

University press

Spears .D.(2006), Developing critical Reading Skills 2B 239999953 Mss 20061.

Wallace .G (1992) Reading oxford.oxford university press.vol 2 No9 817- 822

Wenden.A(1991). Learner strategies for Learner Autonomy: planning and implementing Learner Training for Language Learners.Cambridge;prentice Hall international (UK).

Wiener.H.S.(1997) Reading skills hand Book (7th Ed.)Boston and Newyork: Houghton Mifflin company.

Williams. E (1984) Reading in the Language Classroom. London; MaCmillan Publishers.

Williams, M.and Bureden.R.L (1997) Psychology for language teachers: Asocial Constructivist Approach Newyork: Combridge Cambridge university press.

Willing.Ken. (1989).teaching how to learn learning strategies in ESL. Sudney National center for English Language Teaching and Research.

Zeynali.S.etal(2015)the effects of socio- affective strategy in enhancement of reading comprehension in Iranian EFL learners.International Journal of language and linguistics.Vol.4.No.2-1 2015,pp.9- 22 doi:10.11648/jjj11.s.20160402

# አባሪ አንድ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የሂዩማኒቲስ  ቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሁፍ እና ፎክለር ክፍለ  ትምህርት
## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በብርሃነ ህሊና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትእና ሆሊሲቨር ትምህርት ቤቶች "የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበርን በንጽጽር መፈተሽ  "በሚል ርእስ የሚካሄደው ጥናት መምህራን በክፍል ውስጥ ትምህርቱን ሲያከናውኑ ለመከታተያነት የተዘጋጀ የምልከታ መከታተያ ቅጽ

**ክፍል አንድ**

1. የትምህርት ቤቱ ስም ------------------

2. የመ/ሩ/ሯ መለያ ኮድ ---------------

3. የትምህርት ደረጃ ----------------

4. ምልከታው የተካሄደበት ክፍል--------------

5. የትምህርት ርእስ -------------

6. ቀን --------------

7. የምልከታ ጊዜ 1ኛ -------- 2ኛ --------- 3ኛ -------4ኛ

8. የአንዱ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ --------------

9. የእለቱን ትምህርት በተመለከተ መ/ሩ/ሯ የትምህርቱን የትምህርት ዕቅድ

አዘጋጅተዋል-------- ☐  አላዘጋጁም--------- ☐

10. መምህሩ/ሯ የትምህርቱን አላማ አስተዋዉቀዋል ----------- ☐
አላስተዋዉቀዋል  ----------- ☐

**ክፍል ሁለት**

ቀጥለዉ መምህራን በክፍል ዉስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ መከናወን የሚገባቸዉ ነጥቦች መከናወን አለመከናወናቸዉን ለመመልከት “ተከናዉኗል” እን “አልተከናወነም” የሚሉ አማራጮች ቀርበዋል፡፡ በይዘቶቹ ፊት ለፊት በአማራጮቹ ግርጌ የ (✓) በመጠቀም አስቀምጥ/ጪ

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ/ቁ</th><th rowspan="2">መምህሩ/ሯ በክፍል ዉስጥ አንብቦ መረዳት ብልሀቶች ተጠቅመዉ በሚያስተምርበት ወቅት የሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት</th><th colspan="2">የአተገባበር ሁኔታ</th></tr>
<tr><th>ተከናዉኗል</th><th>አልተከናወኑም</th></tr>
<tr><td>1</td><td>የንባቡን ርዕስ ዓላማ በግልፅ የማስቀመጥ ፣ የማብራራትና መተንተን ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>2</td><td>የተማሪዎች ቅድመ ዕዉቀት ወይም ክህሎት ከህይዎት ልምዳቸ ጋር በማጣጣም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ለተማሪዎች በመስጠት የህሳብ ማፍለቅ ብልሀትን በመጠቀም በቡድንና በተናጠል እንዲሰሩ የመቀስቀስ ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>3</td><td>ምንባቡ ከመነበቡ በፊት በምንባቡ ዉስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትና ሀረጋትን ለተማሪዎች በሰሌዳ ላይ በመፃፍና በማስተዋወቅ ትርጉማቸዉን እንዲገምቱና እንዲተነብዩ የማድረግ ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>4</td><td>ምንባቡ ስለምን እንደሆነ በአጭሩ ለተማሪዎች ማስተዋወቅ ወይም ተገቢ የሆነ ፍንጭ የመስጠት ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>5</td><td>ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፍ የቀረቡ የንባብ ክሂል ይዘቶችን በክፍል ዉጥ ሲተገብሩ ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ተጠቅመዉ የማስተማር ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>6</td><td>ለተማሪዎች አንብቦ መረዳትን ሲያስተምሩ ድምፅን ከፍ አድርጎ የማንበብ ብልሃትን ተጠቅመዉ እንዲያነቡ የማነሳሳትና ከአነበቡት ምንባብ ዉስጥ ዋና ሀሳብ ነጥለዉ እንዲያወጡ የማበረታታት ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>7</td><td>ለተማሪዎች ምንባብ ሲያነቡ ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትንእንዲጠቀሙ የማበረታትና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሲመልሱ ምክንያታዊ ብልሃትን በመጠቀም እንዲመለሱ የማድረግ ሁኔታ</td><td></td><td></td></tr>
</table>

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | ተማሪዎች ስለሚያነቡት ምንባብ ምስል የመከሰት ብልሃቶችን ተጠቅመዉ ምስል እየፈጠሩ እንዲያነቡ የማድረግ ሁኔታ | | |
| 9 | ተማሪዎች በቅድመ ንባብና በንባብ ጊዜ የአንድምታና ትንብያ ብልሃትን በመጠቀም እንዲተነብዩና እንዲገምቱ አድርጎ የማስተማር ሁኔታ | | |
| 10 | ተማሪዎች ምንባብን በሚያነቡበት ጊዜ ደጋግሞ የማንበብ ብልሃትን በመጠቀም የምንባቡ መንስዔና ዉጤት፣እዉነታና አስተያየት እንዲሁም የነገሮችን አንድነትና ልዩነት እንዲለዩ አድርጎ የማስተማር ሁኔታ | | |
| 11 | ተማሪዎች ሲያነቡ የማጠቃለያና የመደምደሚያ ብልሃትን እየተጠቀሙ እንዲያነቡ የማስተማር ሁኔታ | | |
| 12 | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ለመተግበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች የየራሳቸዉን ሚና የመወጣት ሁኔታ | | |
| 13 | ተማሪዎች ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ሀሳቡን በፍጥነት የማግኘት ብልሃትን በግርፍና በአሰሳ ምንባብ ተጠቅመዉ እንዲያገኙ አድርጎ የማስተማር ሁኔታ | | |
| 14 | በተማሪዉ መፅሀፍ ዉስጥ የተካተቱ ይዘቶችን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በመተግበር ያላቸዉን ተስማሚነት አጢኖ መጠቀም | | |
| 15 | ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ የማብራራት ፣ የመተርጎምና መተንተን ብልሃትን በመጠቀም እንዲያብራሩና እንዲተነትኑ የማድረግ ሁኔታ | | |
| 16 | በድህረ ንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ምንባቡ እንዳለቀ ተማሪዎች ስላነበቡት ነገር እንዲተነትኑና እንዲያብራሩ የማድረግ ሁኔታ | | |
| 17 | ተማሪዎች ምንባቡን ሲያነቡ በቅድመንባብ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ ጊዜ የሚያጋጥሟቸዉን አዳዲስ ቃላትና ሀረጋትን የመግለፅ ሁኔታ | | |
| 18 | ተማሪዎች ምንባቡን አንብበዉ ከጨረሱ በኃላእርስ በርሳቸዉ ስለአነበቡት ምንባብ እንዲወያዩ፣ እንደገና እንዲናገሩ እና ሀሳባቸዉን እንደገና እንዲያደራጁ አድርጎ የማስተማር ሁኔታ | | |

# አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሁፍ እና ፎክለር ክፍለ ትምህርት
## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የፅሑፍ መጠይቅ

መግቢያ

ውድ ተማሪዎች የዚህ ፅሁፍ መጠይቅ ዋና አላማ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩየ8ኛክፍል "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥአተገባበርን በንጽጽር መፈተሽ፤ በሚል ርእስ ለሚቀርበው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም መጠይቁን በምትሞሉበት ጊዜ ማንንም ሰው ሳታማክሩ በመመለስና ለምትሰጡት መልስ ታማኝ በመሆን ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት የበኩላችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አስፈላጊ አይደለም ፤ ለመጠይቁ መልስ በመስጠታችሁ በእናንተ ወይም በትምህርት ቤታችሁ ላይ የሚያመጣው ምንም ችግር እንደሌለ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም ውደ የትምህርት ጊዜያችሁን መስዋት በማድረግ ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

የትምህርት ቤቱ ስም --------------------

ፆታ -------------

ክፍልና ሴክሽን --------------

የትምህርት ዘመን ---------------

ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ዉስጥ አተገባባርን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርሶም ጥያቄዎቹን በአግባቡ ካነበቡ በኃላ ለመልስነት ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ በይዘቶቹ ፊት ለፊትና ከአማራጮቹ በታች (✓) ምልክት አስቀምጡ፡፡ አማራጮቹም 5.በጣም ከፍተኛ 4.ከፍተኛ 3.መካከለኛ 2.ዝቅተኛ 1. በጣም ዝቅተኛ የሚሉ ናቸዉ፡፡

| ተ/ቁ | የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የቀረቡ የተለያዩ ጥያቄዎች | አማራጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በ.ዝቅተኛ |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የምንባቡን ርዕስና አላማ በግልፅ የማብራራት፣ የመተንተንና የመተርጎም ሁኔታ | | | | | |
| 2 | ምንባቡን ከመጀመራችሁ በፊት ከቅድመ ዕዉቀታችሁ ወይም ከህይወት ልምዳችሁ ጋር በማጣጣምና በማገናዘብ ሀሳብ ማፍለቅ ብልሃትን በመጠቀም ቅድመ ግምት እንዲሰጡ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 3 | ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ምንባቡ ዉስጥ ያሉአዳዲስ ቃላትና ሀረጋትን ለተማሪዎች በሰሌዳ ላይ በመፃፍና በማስተዋወቅ ትርጉማቸዉን እንዲገምቱና እንዲተነብዩ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 4 | ምንባቡ ስለምን እንደሆነ በአጭሩ ለተማሪዎች ማስተዋወቅ ወይም ተገቢ የሆነ ፍንጭ የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 5 | በመማሪያ መፅሀፍ የቀረቡ የንባብ ክሂል ይዘቶችን በክፍል ዉስጥ ስትማሩ ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ተጠቅመዉ የማስተማር ሁኔታ | | | | | |
| 6 | አንብቦ መረዳትን ስትማሩ ድምፅን ከፍ አድርጎ የማንበብ ብልሃትን ተጠቅማችሁ እንድታነቡ ማድረግና ከአነበባችሁት ምንባብ ዉስጥ ዋና ሀሳብ ነጥላችሁ እንድታወጡ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 7 | ምንባብ ስታነቡ ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትን እንድትጠቀሙ ማድረግና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ስትመልሱ ምክንያታዊ ብልሃትን በመጠቀም እንድትመልሱ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 8 | ስለምታነቡት ነገር ምስል የመከሰት ብልሃትን ተጠቅመዉ ምስል እየፈጠሩ እንድታነቡ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 9 | በቅድመ ንባብና በንባብ ጊዜ አንድምታና ትንብያ ብልሃትን በመጠቀም እንድትነብዩና እንድትገምቱ አድርጎ የማስተማር ሁኔታ | | | | | |
| 10 | የምታነቡትን ንባብ ደጋግሞ የማንበብ ብልሃትን በመጠቀም የምንባቡ እዉነታና አስተያየት እንዲሁምየ ነገሮችን አንድነትና ልዩነት እንድትለዩ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 11 | ምንባብ ስታነቡ የማጠቃለያና | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመደምደሚያ ብልሃትን እንድትጠቀሙየማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 12 | በተማሪዉ መፅሀፍ ዉስጥ ከተካተቱ ይዘቶች እና መልመጃዎች በየትኛዉ አንብቦ መረዳት ብልሃት ማስተማር ተስማሚ መሆኑን አቅዶና አጢኖ የመጠቀም ሁኔታ | | | | | |
| 13 | ተማሪዎች ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ መረጃን የመፈለግ ብልሃትን እንዲጠቀሙ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 14 | በተማሪዉ መፅሀፍ ከተካተቱ ይዘቶች ዉስጥ ተማሪዎች የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃትን በመጠቀም እንዲያብራሩና እንዲተረጉሙ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 15 | ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ የማብራራት ፤የመተርጎምና መተንተን ብልሃትን በመጠቀም እንዲያብራሩና እንዲተነትኑ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 16 | ምንባቡን አንብባችሁ ከጨረሳችሁ በኃላ የሚና ጨዋታ ብልሀትን እንድትጠቀሙ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 17 | ምንባቡን አንብባችሁ ከጨረሳችሁ በኃላ በድህረ ንባብ ጊዜ ግራፍ የማደራጀት ብልሃትን በመጠቀም የፅሁፉን ሀሳብ እንድትገልፁ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 18 | ምንባቡን አንብበዉ ከጨረሱ በኃላ እርስ በርሳቸዉ ስለአነበቡት ምንባብ እንዲወያዩ፣ እንደገና እንዲናገሩ እና ሀሳባቸዉን እንደገና እንዲያደራጁ አድርጎ የማስተማር ሁኔት | | | | | |

# አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሁፍ እና ፎክለር ክፍለ ትምህርት
## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለመምህራን የቀረቡ የቃለ- መጠይቅ ጥያቄዎች

በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ በመሆንዎ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና አላማ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የ8ኛክፍል “የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በንጽጽር መፈተሽ” ለሚለው ጥናት መረጃ ማሰባሰብ ነው፡፡ ስለሆነም ርስዎ የሚሰጡት ትክክለኛ ና እውነተኛ ምላሽ ለጥናቱ ወሳኝ ስለሆነ ለማቀርብልዎ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት እንዲተባበሩኝ በትህትና እጠይቃሁ፡፡

- የመምህሩ የትምህርት ደረጃ ----------
- ፆታ --------------
- የአገልግሎት ዘመን ----------------
- ዕድሜ --------------

**ጥያቄዎች**

1. በማስተማር ሙያ ላይ እያሉ የአንብቦ መረዳ ብልሃቶች አተገባበርን በተመለከተ የስራ ላይ ስልጠና አግኝተዉ ያዉቃሉ? አግኝተዉ ከሆነ ምን ጥቅም አገኙበት
2. የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ክሂል ለማሻሻል ምን ምን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተጠቅመዉ ያስተምራሉ ?
3. የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ተማሪዎች የሚማሩትን የአንብቦ መረዳት ትምህርት የሚጠበቀዉን ዉጤት ለማምጣት ይጠቅማል ብለዉ ያምናሉ?
4. እርሶ በክፍል ዉስጥ ሲያስተምሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳ ትጠቀሙ የሚያደርግዎት ችግሮች አሉ? ካሉ ይዘርዝሩ ?